
# አዲስ ልሳን

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

ቅጽ 32 ቁጥር 3575 | ቅዳሜ ግንቦት 22 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር








# በአንድ ካርድ ብዙ ቁምነገር

5




የዘንድሮን ጨምሮ ባለፉት ጠቅላላ ምርጫዎች የምርጫ ካርድ የወሰዱ መራጮች ቁጥር

## ተረጅነትን የተፀየፉ እጆች

6



ፎቶ-በገነት ወንድሙ

በሴፍቲኔት መርሐ ግብር መስሪያ ቦታ ተሰጥቷቸው በባልትና ውጤታማ የሆኑት ወ/ሮ አዝመራ ጐበዜ

## በሚሊዮኖች ስክሪን ላይ የበራችው ኢትዮጵያ

10



ፎቶ- ከገፀ ድር

ባሳለፍነው ሳምንት የኢትዮጵያ ጉብኝቱን አጠናቅቆ ወደ ሀገሩ የተመለሰው ዴላን ፔጅ

## በአረንጓዴ ሜዳ ላይ የፈካው ተስፋ



19

ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ ተገንብተው ወደ አገልግሎት ከገቡ አዳዲስ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች መካከል አንዱ

# ነዋሪዎችን ከኑሮ ውድነት የታደጉ ማዕከላት

### “በከተማዋ በሮች የተገነቡ የገበያ ማዕከላት ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ወገኖች ከፍተኛ እፎይታ ፈጥረዋል” ሸማቾች

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በግምት ዕድሜአቸው በአምሳዎቹ መጀመሪያ የሚገኙ የሚመስሉት ወይዘሮ የየሺወርቅ ደበላ፣ የአዲስ አበባን የገበያ ፈተናዎች ጠንቅቀው ያውቁታል። ላለፉት 20 ዓመታት በቆዩባት አዲስ አበባ ወደ ገበያ በሄዱ ቁጥር የሚቀበላቸው የሸቀጦች መወደድ፣ የምርት ጥራትና የአቅርቦት ጉድለት ብቻ አልነበረም፤ በአምራቹና በሸማቹ መካከል ቆሞ የላባቸውን ፍሬ የሚመነትፈው የደላላው ረጅም እጅም ጭምር እንጂ።

ወይዘሮ የየሺወርቅ ያለፈውን የኑሮ ትግል በትዝታ እያሰቡ፣ “አትክልቱ፣ ጥራጥሬው፣ ሁሉም ነገር እጃችን ላይ ከመድረሱ በፊት በአራትና በአምስት ደላላ በኩል

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ፎቶ- ከፋይል

በአቃቂ ቃሊቲ የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከል ግብይት ሲፈጸም

# የአዲስ አበባ እንቅልፍ አልባ ትጋት

- **ከተማዋ በአዲስ የሥራ ባህል ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ያገኙ ውጤቶችን ስለማስመዝገቧ ተመላክቷል**

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የዓለምን የኢኮኖሚ ካርታ የቀየሩ ታላላቅ ከተሞች አንድ የጋራ ምስጢር አላቸው። እሱም ፀሐይ ስትጠልቅ ሥራን አለማቆማቸው ነው። እንደ ኒው ዮርክ የሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ግንባታና የንግድ ልውውጥ፣ እንደ ቶኪዮ እና ሴኡል ያሉ ከተሞች ደግሞ በቴክኖሎጂና በኢንዱስትሪ ዓለም አቀፍ የበላይነትን ያገኙት፣ ከተማቸውን ለ24

ወደ ገጽ 4 ዞሯል





**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ




## ምርጫ ለሀገር ዘላቂ ሰላምና እድገት ወሳኝ ነው!

ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የየትኛውም ሀገር የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ የህዝብ ፈቃድ መሆኑን የሚያረጋግጥ የላቀ አስተዳደራዊ እሴት ነው። ስልጣን በምርጫ ሲወሰን እና የፖለቲካ ተዋናዮች ይህንን የህዝብ ድምፅ በቅንነትና በክብር ሲቀበሉት፣ የሀገር ሁለንተናዊ እድገት በዘላቂነት ይረጋገጣል። በምርጫ አማካኝነት የሚመሰረት መንግስት የህዝብን ድጋፍ ታጥቆ ስለሚነሳ፣ ትኩረቱ ሙሉ ለሙሉ በሀገር ልማትና በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ላይ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ የፖለቲካ መረጋጋት ዜጎች ወደ ልማት ሥራዎች በጋራ እንዲሰማሩ የሚያደርግ፣ የሀገርን የብልፅግና ጉዞ የሚያፋጥን እና የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ አስተማማኝ መሰረት ነው።

ምርጫ፣ የዴሞክራሲ ግንባታው ዋነኛ ምሰሶ ነው። የህዝብ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የመንግስት ኃላፊነት በምርጫ ሂደቱ ውስጥ የሚገለጥ ሲሆን፣ ስርዓቱ እንዲጠናከር የሁሉም ወገኖች ተሳትፎ ወሳኝ ነው። የቅድመ ምርጫ፣ የምርጫ ዕለት እና የድህረ ምርጫ ወቅቶች የዴሞክራሲያዊ ባህል መለኪያ ናቸው። ካለፉት ተሞክሮዎች በመማርና ከስህተቶች በመራቅ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የራሳቸውን ድርሻ መወጣት የሁሉም ዜጋና ተቋማት ድርሻ ነው። የምርጫ ሂደት ከአንድ ወቅት ክስተትነት በላይ፣ የሀገርን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስን ታሪካዊ ክንውን መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ሰባተኛውን ጠቅላላ ምርጫ በማከናወን ላይ ትገኛለች። የቅድመ ምርጫው ሂደት እየተገባደደ ሲሆን፣ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች ያሳዩት ስልጡን የክርክር መንገድና መከባበር የሚያበረታታ ነው። የስልጣን ባለቤት የሆነውን መራጭ ህዝብ የሚያከብር የፖለቲካ እንቅስቃሴ መታየቱ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ትልቅ ተስፋ ነው። የፊታችን ሰኞ ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም ደግሞ፣ 57 ሚሊዮን መራጮች በካርዳቸው የሀገሪቱን የነገ ተስፋ የሚወስኑበት ወሳኝ ቀን ነው። ዜጎች በዚህ ታሪካዊ ዕለት፣ የጀመሩትን ሰላማዊ የዴሞክራሲ ጉዞ በድምፅ አሰጣጣቸው ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

የምርጫ ዕለት ዜጎች ህግና ስርዓትን በማክበር፣ በሰላማዊ መንገድ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች በመሄድ ድምፃቸውን የሚሰጡበት ነው። እያንዳንዱ ድምፅ ለሀገር ትልቅ ዋጋ አለው። የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ሰላማዊ መሆን፣ የሀገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ገፅታ ለዓለም የሚያስተዋውቅ፣ ለቀጣይ ትውልድ ደግሞ ጠንካራ የዴሞክራሲ መሰረት የሚጥል ይሆናል።

ከምርጫው በኋላ የሚኖረው ጊዜ ደግሞ፣ የድምፅ ውጤትን በጨዋነት የመቀበልና የጋራ የሀገር ግንባታ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ ጊዜ ነው። የህዝብ ድምፅ የዴሞክራሲ መደምደሚያ ሳይሆን የሀገር ግንባታ ሂደት አንዱ ክፍል ነው። ምርጫው ሲጠናቀቅ፣ አሸናፊውም ሆነ ተሸናፊው ወገን፣ ለሀገር አንድነትና ለጋራ ጥቅም የሚሰሩበት መድረክ መፈጠር አለበት። የጋራ ስምምነትና ብሄራዊ መግባባት የዴሞክራሲ ስኬቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለው ሰባተኛው ጠቅላላ ምርጫ ለሀገር ዘላቂ ሰላምና እድገት ወሳኝ ነው። የምርጫው ስኬታማነት የሚለካው በሂደቱ ሰላማዊነትና በውጤቱ የህዝብ ድምፅ መከበር ነው። ሁሉም ዜጋ፣ የፖለቲካ ፓርቲና መንግስት የየራሱን ኃላፊነት በመወጣት፣ ለሀገር ብልፅግና የሚታገልበትን ታሪካዊ አጋጣሚ መጠቀም ይኖርበታል። ኢትዮጵያ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የጀመረችውን የለውጥ ጉዞ አጠናክራ በመቀጠል፣ ለቀጣዩ ትውልድ የበለጸገች ሀገር የማስረከብ ኃላፊነት አለባት። ሰኞ ዕለት በምርጫ ሳጥን ውስጥ የምናኖረው ድምፅ፣ የኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ የሚያጠናክር ነው!

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ እመርታ በአፍሪካ ሰማይ ስር!

**በቱም ቱም ሌንጮ**

ኢትዮጵያ ለ7ኛው ሀገራዊ ምርጫዋ ዋዜማ፣ ዜጎች በሰከነ መንፈስ ውሳኔያቸውን በሚያመዛዝኑበት ታሪካዊ የጥሞና ወቅት ላይ ትገኛለች። 57 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዜጎችን ለመራጭነት በመመዝገብም በአፍሪካ የፖለቲካ ታሪክ አዲስና ደማቅ ምዕራፍ እየጻፈች ነው።

ባለፉት የለውጥ ዓመታት ለነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲሁም ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መጎልበት የተከናወኑ ተግባራት ለዚህ ስኬት ዋነኛ ምሰሶዎች ናቸው። የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በገለልተኝነት መዋቀሩ፣ የዴሞክራሲያዊ ምህዳሩ በነጻነት መንፈስ መስፋቱ እና የተፎካካሪ ፓርቲዎች ንቁ ተሳትፎ ሂደቱን ይበልጥ አግዘውታል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ የዜጎች ከወትሮው የተለየ በሀገር ጉዳይ ላይ የባለቤትነት ስሜት መዳበር፣ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ተነሳሽነት መጨመር፣ የምሁራን ስልጡን የፖለቲካ ትንተና እና አማራጭ የ"ቢሆን" መፍትሄዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እውቀትና ሃሳብን መሠረት አድርገው ያካሄዷቸው የምርጫ ክርክሮች፣ ፍጹም ሰላማዊና ስልጡን የነበረው የምረጡኝ ቅስቀሳ እንዲሁም የሚዲያው ሚዛናዊና ንቁ ሚና ለዚህ ታላቅ ሀገራዊ ክንውን ተጨማሪ ድምቀት ሆነዋል። መራጩ ህዝብ በቁጥር ደረጃ ሲታይ፣ በአህጉሪቱ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ካላቸው ጥቂት ሀገራት ተርታ የሚሰለፍ መሆኑ፣ ሀገሪቱ የጀመረችውን የዲሞክራሲ ሥርዓት የማጽናትና ተቋማትን የመገንባት ታሪካዊ ጉዞ በእጅጉ ያፋጥነዋል።

ይህ ታሪካዊ ወቅት፣ ኢትዮጵያ ብሎም መላው አፍሪካ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ተገዥና ተመልካች ብቻ ሳይሆኑ፣ የራሳቸውን እጣ ፈንታ በራሳቸው መወሰን የሚችሉ ግንባር ቀደም ተዋናዮች መሆናቸውን ለመላው ዓለም በተግባር ያረጋገጡበት ደማቅ አጋጣሚ ሆኖ በታሪክ መዝገብ ላይ ይሰፍራል።

ይህ ታላቅ ህዝባዊ ንቅናቄ፣ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ በጦር አፈሙዝ ስሌት ወይም በሴራ ሳይሆን፣ በዜጎች ንቁ ተሳትፎና በሚስጥር በሚሰጥ የምርጫ ካርድ ብቻ የሚወሰን መሆኑን በፅኑ ያበስራል።

የመራጩ ቁጥር በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 38 ነጥብ 2 ሚሊዮን አሁን ወደ 57 ነጥብ 4 ሚሊዮን ማደጉ፣ ለሰለጠነና ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር አስተማማኝ መሠረት የሚጥል ታሪካዊ እመርታ ከመሆኑም በላይ፣ ለነገዋ የበለጸገችና የተረጋጋች ኢትዮጵያ የማይናወጥ የሰላም ዋስትና ነው።

ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ነዋሪዎችን ... ከገጽ 1 የዞረ

ያልፋል። አምራቹ ዝቅተኛ ትርፍ ሲያገኝ፣ እኛ ሸማቾቹ ደግሞ በውድ ዋጋ እንበዘበዝ ነበር” ይላሉ፡፡

ይህ በከተማዋ ስር ሰዶ የቆየው ያልተዘመነ የንግድ ሥርዓት ግን ዛሬ ወይዘሮ የየሺወርቅን ከመሰሉ አያሌ እናቶች ትከሻ ላይ ወርዷል፤ ምክንያቱም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማዋ መግቢያና መውጫ በሮች ላይ የገነባቸው የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከላት፣ የደላላውን ረጅም እጅ ቆርጠውታል። በተለይም በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የተገነባው ማዕከል፣ ለወይዘሮ የየሺወርቅ አዲስ ተስፋና የእፎይታ ምንጭ ሆኖላቸዋል።

ወይዘሮ የየሺወርቅን በአቃቂ ቃሊቲ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከል ስናገኛቸው ፊታቸው በደስታ መንፈስ ተሞልቶ ነበር። የገበያ ቦርሳቸውን በትኩስ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች ሞልተውታል። “ይህ ማዕከል ለእኛ ለእናቶች የነፍስ ማደሪያ ነው” ይላሉ በፈገግታ። “ቀደም ሲል ቃሊቲ፣ ሳሪስ፣ ወይም መርካቶ ድረስ ሄደን የምንፈልገውን ለማግኘት ሙሉ ቀን ይፈጅብን ነበር። ዋጋውም እንደ አየሩ ፀባይ ይዋዥቃል። አሁን ግን በአንድ ጣራ ስር ሁሉንም ነገር አገኘን።”

እንደ ወይዘሮ የየሺወርቅ ምስክርነት፣ የማዕከሉ ዋነኛ ትሩፋት ምርቶቹ ያለምንም ደላላ ጣልቃገብነት በቀጥታ ከአምራቾች እጅ ለሸማቾች መቅረባቸው ነው። ይህ አሰራር ከሌሎች የተለመዱ የከተማዋ ገበያዎች አንጻር ከ15 እስከ 20 በመቶ የሚደርስ የዋጋ ቅናሽ አስገኝቷል።

በተመሳሳይ በለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከል ግብይት ሲፈፅሙ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሉባባ ሽኩር፣ በየቀኑ የሚስተዋለው የገበያ አለመረጋጋት የሚያሳስባቸው የቤት እመቤት እንደሆኑ ይናገራሉ። በተለይም ሽንኩርት፣ ድንችና አትክልት ለመግዛት በአቅራቢያቸው ወዳሉ የመንደር ውስጥ ሱቆች ጎራ ባሉ ቁጥር በዋጋው መናር ልባቸው መሸበሩ አይቀሬ ነበር። ዛሬ ግን የተለመደውን የመንደራቸውን ሱቅ አልፈው ወደ ለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከል በማቅናት የፈለጉትን ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

ወይዘሮ ሉባባ በመንደር ገበያዎች በ100 እና በ120 ብር የሚሸምቱትን አንድ ኪሎ ሽንኩርት በለሚ ኩራ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከል በ80 እና በ60 ብር፣ ከውጭ በውድ የሚገዙትን አንድ ኪሎ ድንች ደግሞ በ30 ብር ብቻ መግዛታቸውን ጠቁመው፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱን ማግኘታቸው ትልቅ እፎይታ እንደሰጣቸው ገልፀውልናል፡፡

የወይዘሮ ሉባባ እና የየሺወርቅ ታሪክ የሺዎች የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የዕለት ተዕለት ትግል ማሳያ ነው። አዲስ አበባ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ፣ በየእለቱ የሚገቡና የሚወጡ እንግዶች የሚርመሰመሱባት ሰፊ ከተማ ነች። አልፎ ተርፎም መዲናዋ ዓለም አቀፍና የዲፕሎማሲ ከተማ እንደመሆኗ፣ ባላት ሰላምና ፈጣን እድገት ምክንያት



ፎቶ- ከገፀ ድር

የለሚ ሁለገብ ገበያ ማዕከል ከፊል ገጽታ

የበርካታ የውጭና የሀገር ውስጥ እንግዶች መዳረሻ ሆናለች። ይህ ተለዋዋጭና እያደገ የመጣው የህዝብ ቁጥር ደግሞ በከተማዋ ትልልቅ የገበያ ማዕከላትን መገንባትና የኑሮ ውድነትን ለማስታገስ የሚያስችሉ ዘመናዊ የገበያ ሥርዓቶችን መዘርጋት የግድ አስፈላጊ እንዲሆን አድርጎታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይህን እውነታና የህዝቡን እንግልት በመገንዘብ፣ የገበያ ሥርዓቱን ለማስተካከልና አምራችና ሸማቹን በቀጥታ ለመገናኘት የሚያስችሉ የግብይት ማሻሻያዎችን ማድረግ ከጀመረ ቆይቷል። በከተማዋ ዋና ዋና መውጫና መግቢያ በሮች እንዲሁም ከፍተኛ የህዝብ ብዛት ባላቸው ሰፈሮች ትልልቅ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የሰብሎች እና የኢንዱስትሪ ምርቶች መገበያያ ማዕከላት ደረጃቸውን በጠበቀ መንገድ ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል።

ከእነዚህም አንዱ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ተገንብቶ ወደ ሥራ የገባው የገበያ ማዕከል ነው። ማዕከሉ የኑሮ ውድነት ጫናን በመቀነስ ረገድ ለማህበረሰቡ ትልቅ እፎይታን እየፈጠረ እንደሚገኝ ሸማቾች ያረጋግጣሉ። እንደ ነዋሪዎቹ ገለፃ፣ የከተማ አስተዳደሩ የኑሮ ውድነቱን ጫና ለማስታገስ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች መካከል የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች እንዲሁም በከተማዋ መግቢያ በሮች ተገንብተው አገልግሎት መስጠት የጀመሩ የገበያ ማዕከላት ለሸማቹ ማህበረሰብ አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።

በዚሁ ማዕከል ሲገበያዩ ያገኘናቸው አቶ ወርቁ ከበደ የተባሉ አስተያየት ሰጪ፣ በገበያ ማዕከሉ የተለያዩ ምርቶች በስፋት፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ እየቀረቡ እንደሆነ ይመሰክራሉ። “ይህ የዋጋ ንረትን በመከላከል በተለይ ለዝቅተኛው ማህበረሰብ ከፍተኛ እፎይታ የፈጠረ ሥራ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል” ብለዋል አቶ ወርቁ ከበደ፡፡

የኑሮ ውድነትን ለማቃለል፣ ምርት በብዛት ማቅረቢያ እና የግብይት ማዕከላት ማስፋት ሥራ አካል የሆነው 7ኛው የለሚ ሁለገብ የገበያ ማዕከል በቅርቡ ለአገልግሎት ክፍት መሆኑ ይታወሳል። ማዕከሉ የኑሮ ውድነትን የሚያቃልሉ ዘመናዊ፣ ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ ያላቸው 221 መጋዘኖች፣ የችርቻሮ ሱቆች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ወፍጮ ቤቶች እንዲሁም በአንድ ጊዜ 250 ተሽከርካሪዎችን ማቆም የሚችል ፓርኪንግ ያካተተ ነው። ይህ ማዕከል ለለሚ ኩራ፣ ለቦሌ እና ለየካ ክፍለ ከተሞች ነዋሪዎች በአማካይ ቦታ እና በሰሚት ዋና መንገድ ላይ የሚገኝ ምቹ የሆነ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ነው።

ማዕከሉ ማህበረሰቡ ለዕለት ፍጆታ የሚጠቀምባቸውን የሰብል ምርቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ የበርበሬ፣ የቅመማ ቅመም ምርቶች እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን የአንድ ማዕከል የግብይት ሥርዓት እውን አድርጓል። በማዕከሉ የሚቀርቡ ምርቶች ከውጭ ገበያ ከ15 እስከ 20 በመቶ የዋጋ ቅናሽ የሚሸጡበት፣ ዋጋ የሚያንረውን ሕገ-ወጥ የደላላ ሰንሰለት በመበጣጠስ ከአምራቹ ያልተቋረጠ ምርት የሚቀርብበትና የከተማዋን ነዋሪዎች የኑሮ ጫና የሚያቃልል እንደሆነ ተገልጿል።

ከዚህም ባለፈ ማዕከሉ ማህበራዊ ፍትሕን ያረጋገጠ ነው። በዚህ ገበያ ማዕከል ከተለያየ ቦታ በኮሪደር ልማት የተነሱ ነዋሪዎችንና የገበያ ማዕከሉ ያረፈበትን 3 ነጥብ 2 ሄክታር መሬት ለልማት የለቀቁ አርሶ አደሮች በማዕከሉ ሱቅ እንዲያገኙ ተደርጓል፤ ይህም ለነዋሪዎች ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጥሯል። አዲሱ የለሚ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ቀደም ሲል በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ የነበሩ ስብራቶችን በመጠገን፣ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን በቂ የመኪና መቆሚያና የደህንነት ሁኔታ መኖሩ ለሸማቹም ሆነ ለነጋዴው ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል።

በለሚ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ሲሸምቱ ያገኘናቸው ወይዘሮ ትግስት ተፈራ እንደገለፁት፣ ለዕለት ፍጆታ የሚጠቀሟቸውን የሰብል ምርቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ የበርበሬና የቅመማ ቅመም እንዲሁም ፓስታ፣ ዘይትና ማካሮኒ መሰል የኢንዱስትሪ ምርቶችን በአንድ ማዕከል መሸመት መቻሉ አዲስ ጅምር ነው።

“ምርቶችን በአንድ ማዕከል ማግኘት ብቻ ሳይሆን በአቅርቦት፣ ዋጋና ጥራት አኳያም በእጅጉ የሚያስደስት ነው” ይላሉ ወይዘሮ ትግስት። ለምሳሌ ያህልም ከማዕከሉ ውጪ 2 ሺህ 200 ብር የሚሸጠውን ፈሳሽ ዘይት በማዕከሉ በ1 ሺህ 600 ብር፣ እንዲሁም በውጭ በኪሎ 140 ብር የሚሸጠውን የዳቦ ዱቄት በ110 ብር መግዛታቸውን ይገልጻሉ።

ሌላዋ ሸማች ስምረት ገዛሃኝ በበኩላቸው፣ በገበያው በተለይ ዘይትና እንቁላል ከውጭው ገበያ እጅግ በተሻለ ዋጋ እንደገዙ በመግለፅ፣ የገበያዎቹ በተደራጀ መንገድ ሥራ መጀመር አማራጭ ምርትን በተመጣጣኝ ዋጋ ከመስጠቱ ባሻገር ሁሉንም ፍላጎቶች በጥራት ለማሟላት አመቺ እንደሆነ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።

የገበያ ማዕከሉ ለሸማቹ ብቻ ሳይሆን ለወጣት ነጋዴዎችም አዲስ ተስፋ ሆኗል። በገበያ ማዕከሉ ወተትና የወተት ተዋፅኦ መሸጫ ሱቅ ከፍታ የምትሠራው ወጣት ቃልኪዳን አበራ፣ መንግስት ለህዝብ የገባውን ቃል በተግባር ለማሳካት እያደረገ ያለውን ጥረት ታደንቃለች። በጥሩ የኮንስትራክሽን ሥራዎችና በተሟላ መሠረተ ልማት ገበያ መገንባቱ ህዝቡን በተመጣጣኝ ዋጋና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ለመግዛት እንደሚያስችለው ትናገራለች።

እንደ ወጣቷ አስተያየት፣ የገበያ ማዕከሉ በቅርቡ ሥራ የጀመረ ቢሆንም ጥሩ የሆነ የገበያ ሁኔታን እያስተናገደች ሲሆን፣ የያዘቻቸው ምርቶችም ጥራታቸውን የጠበቁና በፅዳት የተዘጋጁ በመሆናቸው በጊዜ ሸጣ ትጨርሳለች። ለወደፊቱም አሳን ጨምሮ ሌሎች የእንሰሳት ተዋፅኦዎችን በስፋት በማስገባት ለማህበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ለማድረግ በትጋት እንደምትሠራ ትገልጻለች።

የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ በበኩላቸው፣ የለሚ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ጨምሮ ሌሎች በከተማዋ በሮች የተገነቡ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች መሸጫ ማዕከላት ቀደም ሲል በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ የነበሩ ስብራቶችን በመጠገን፣ የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

ምርታማነትንና አቅርቦትን በመጨመር የነዋሪውን የኑሮ ጫና ለማቃለል ሰፊ ሥራዎች መከናወናቸውን ያስታወሱት ወይዘሮ ሀቢባ፣ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት አምራችና ሸማችን በቀጥታ ማገናኘት በመቻላቸው አላስፈላጊ የሆኑ ደላሎችንና የንግድ ሰንሰለቶችን ማሳጠር መቻሉን ያሰምሩበታል። ይህም ለከተማዋ ነዋሪዎች የግብርና እና የኢንዱስትሪ ፍጆታ ምርቶችን በስፋትና በውጤታማነት በማቅረብ ጤናማ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር ትልቅ እገዛ አድርጓል።

የገበያ ማዕከላቱ የነዋሪውን የኑሮ ጫና ለማቃለል ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠ ማሳያ መሆናቸውን ያነሱት ቢሮ ኃላፊዋ፣ ማዕከላቱ ፍትሐዊ የገበያ ውድድር ላይ የተመሠረተ አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ በየደረጃው እንደሚደረግም አረጋግጠዋል።

## የአዲስ... ከገጽ 1 የዞረ

ሰዓታት ክፍት በሚያደርግ ጠንካራ የሥራ ባህል ነው። የምጣኔ ሀብት እና የከተማ ጥናት ባለሙያ የሆኑት ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ግሌዘር እንደሚሉት፣ የአንድ ከተማ ዕድገት የሚለካው በሕንፃዎቿ ከፍታ ብቻ ሳይሆን በደቂቃዎች ውስጥ በምትፈጥረው ምርታማነት ጭምር ነው።

የደቡብ ኮሪያዋ ሴኡል ከድህነት ወጥታ የዓለም የኢኮኖሚ ኃያል እንድትሆን ያስቻላት 'ፓሊ-ፓሊ' (Pali-Pali) ወይም "በፍጥነት-በፍጥነት" የሚለው ብሔራዊ የሥራ ባህሏ ነው። ይህ ባህል ፕሮጀክቶች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ፣ ሠራተኞች በፈረቃ እንዲሠሩና በደቂቃዎች ውስጥ ምርታማነት እንዲመዘገብ አድርጓል። በተመሳሳይ እንደ ዱባይ ያሉ ከተሞች በበረሃ ላይ የዓለም የቱሪስትና የንግድ ማዕከል የሆኑት፣ የሌሊቱን ጨለማ በብርሃን ተክተው ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በመጨረሳቸውና ያም የፈጠረው ትርፍ ተመልሶ ወደ ዜጎች ሕይወት እንዲገባ በማድረጋቸው ነው።

ዛሬ አዲስ አበባም ይህንን ዓለም አቀፍ የስልጣኔና የኢኮኖሚ ቀመር በተግባር ማዋል ጀምራለች። ከተማዋ በ7/24 (ሳምንቱን ሙሉ) የሥራ ባህል ውስጥ ስትገባ፣ የፈረቃ ሥራን እንደ አዲስ መተንፈሻ በመጠቀም የሥራ ዕድልን እያሰፋችና በሠሩት ልክ የሚከፈልበትን ፍትሐዊ የሥራ ድባብ እየፈጠረች ነው። ይህ ከዓለም የተቀሰመው ልምድ ፕሮጀክቶች ሳይጓተቱ እንዲጠናቀቁና ውጤታቸውም በዜጎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ላይ ለውጥ እንዲያመጣ እያገዘ ይገኛል።

መዲናዋ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያስመዘገበችው ትልቁ ድል ሜጋ ፕሮጀክቶችን በፍጥነት ማጠናቀቋ ብቻ ሳይሆን፣ ያንን ለማድረግ ያስቻለ 'ጠንካራ የሥራ ባህል' መውለዷ ነው። በፈረቃ መሥራት እንደ ልምድ እየተወሰደ ባለበት በዚህ ወቅት፣ ሥራ ለዜጎች የሚሰጠው ክብርና ክፍያ እንዲሁም ፕሮጀክቶች በፍጥነት ተጠናቅቀው ወደ ሕዝብ አገልግሎት ሲገቡ የሚፈጥሩት ትርፍ፣ ከተማዋን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት እያደረጋት ነው።

አዲስ አበባ አሁን ላይ ምን ትመስላለች የሚለውን በጥልቀት ከመዳሰሳችን በፊት፣ የቀደመ ገጽታዋን በአስረጅነት መጥቀስ ተገቢነት ይኖረዋልና ወደዚያው እንለፍ። ከጥቂት ዓመታት በፊት አዲስ አበባን በምሽት ለሚመለከት ሰው፣ አብዛኞቹ የከተማዋ አካባቢዎች ገና ፀሐይ ሳትርቅ በድንገተኛ ዝምታ የምትዋጥ (ቀድማ የምትተኛ) መዲና ነበረች። የትራንስፖርት ዘርፉ ምሽት ሁለት ሰዓት ሳይሞላ ጭር ማለታቸውና በጨለማ መዋጣቸው፣ የከተማዋን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለግማሽ ቀን ብቻ የተገደበ እንዲሆን አድርጎት ቆይቷል። በወቅቱ የነበረው የመንገድ መሠረተ ልማት ችግር፣ የመብራት እጥረትና የደህንነት ሥጋት፣ የ24/7 የሥራ ባህልን ቀርቶ በምሽት በነፃነት መንቀሳቀስን እንኳ የማይታሰብ ሕልም አድርጎት ነበር።

የመገናኛ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ስለሺ ይገዛው የከተማዋ ወንዞች ዳርቻዎችን፣ እንደ የቂርቆስ፣ የአራት ኪሎ እና የቸርችል ጎዳና ግርጌዎችን ለአብነት በመጥቀስ በሰጡት አስተያየት፤ አስከፊ ጠረን የሚወጣባቸው፣ በቆሻሻ የተሞሉና ለወንጀል ድርጊቶች ምቹ መደበቂያ የነበሩ ስፍራዎች እንደነበሩ ያስታውሳሉ። "እነዚህን አካባቢዎች ጠንቅቄ አውቃቸዋለሁ" ይላሉ።

አቶ ስለሺ ሐሳባቸውን ሲቀጥሉም፣ እነዚህ አካባቢዎች ለልማትና ለሥራ ከመዋል ይልቅ የከተማዋ የማይነኩ ቁስሎች ሆነው መቆየታቸው የዜጎችን የመሥራት ተነሳሽነት ከመግደሉም በላይ፣ ፕሮጀክቶች ቢጀመሩ እንኳ ለዓመታት ተጓትተው ለብክነት ይዳረጉ ነበር ሲሉ ያክላሉ።

ዛሬ ግን ያ ታሪክ በአዲስ ምዕራፍ ተተክቷል። በአሁኑ ሰዓት በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት በመገናኛ፣ በሲኤምሲ፣ በቦሌ እና በፒያሳ አካባቢዎች የሚታየው እውነታ የትናንቱን ድቅድቅ ጨለማ በብርሃን የለወጠ ነው። ማሽኖች ሌሊቱን ሙሉ ሲቆፍሩና ሲገነቡ፣ ሠራተኞች በፈረቃ እየተቀያየሩ ሲረባረቡ ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህ የንቁ ከተማ እንቅስቃሴ ደግሞ ቀደም ሲል ለሥራ ምቹ ያልነበሩ አካባቢዎችን ወደ ግዙፍ የሥራ ቦታነት ቀይሯቸዋል። ፕሮጀክቶች ሳይጓተቱ በፍጥነት መጠናቀቃቸው፣ በየአካባቢው ለሚገኙ ወጣቶች ሰፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠሩም በላይ፣ በሠሩት ልክ የሚከፈሉበት አዲስና ግልጽ አሠራር እንዲሰፍን አድርጓል። ትናንት ቆሻሻ ይጣልባቸው የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች ዛሬ በሰው ኃይልና በልማት ደምቀው ሲታዩ፣ የ7/24 የሥራ ባህል በከተማዋ የኢኮኖሚ ደም ሥር ውስጥ ምን ያህል ትርፍ እያፈሰሰ መሆኑን በተግባር ያሳያሉ።

አዲስ አበባ ዛሬ ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላም እንደ ቀኑ የምትነቃቃ ከተማ ሆናለች። የከተማዋ በርካታ አካባቢዎች የ24 ሰዓት የኢኮኖሚ ሞተር ማሳያ ሆነዋል። ቀደም ሲል ለመዝናኛ ብቻ ይታወቁ የነበሩት እንደ ቦሌ፣ ሳር ቤት፣ ሀያ ሁለት የመሳሰሉ አካባቢዎች፣ አሁን ላይ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ በፈረቃ ከሚሰጡት አገልግሎት ባለፈ፣ የንግድ ማዕከላትና የቴክኖሎጂ ቢሮዎች መብራታቸውን ሳያጠፉ የሚያድሩባቸው ንቁ ሰፈሮች ሆነዋል። በአትላስ እና በቦሌ መስመር የሚታየው የትራፊክ እንቅስቃሴና የንግድ ፍሰት፣ ከተማዋ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በምሽት የምታመነጨው ገቢ ከቀኑ ጋር እየተቀራረበ ስለመምጣቱ ግምት መውሰድ ይቻላል።

የመንግሥትና የግል ተቋማት አገልግሎታቸውን ወደ ምሽት በማራዘማቸው፣ ነዋሪዎች በቀን ሥራ ሳይቆራረጡ በምሽት ጉዳያቸውን እንዲያስፈጽሙ አስችሏል። ይህ "የምሽት ኢኮኖሚ" (Night-time Economy) የከተማዋን የሀብት ስርጭትም ፍትሐዊ እንዲሆን አድርጎታል። ባለሙያዎች እንደሚጠቁሙት፣ እነዚህ አካባቢዎች 24 ሰዓት ክፍት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች በሠሩት ሰዓትና በሰጡት ውጤት ልክ ክፍያ የሚያገኙበት (Performance-based) አሠራር መስፈኑ፣ አዲስ አበባን በአፍሪካ ተወዳዳሪና ቀልጣፋ መዲና እያደረጋት ይገኛል።

ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን ሐሳባቸውን ያካፈሉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ እና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰበሃዲን ሱልጣን እንደገለጹት፣ ከዚህ በፊት እንደ ከተማ በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ትልቅ ችግር ሆነው ከሚጠቀሱ ነገሮች መካከል የሥራ ባህል ዋናው ማነቆ ነበር። አሁን ግን በከተማዋ እየተሠሩ ባሉ ፕሮጀክቶች እየተለመደ የመጣው የቀንና የሌሊት ሥራ (7/24) ትልቅ ተሞክሮ ሆኖናል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ይህንኑ የመዲናዋን አዲስ የሥራ ባህል አስመልክተው ሲናገሩ፣ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስ እና እንደ አፍሪካ መዲናነቷ ደግሞ ተወዳዳሪ ለማድረግ የ7/24 የሥራ መርኃ ግብር አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን አፅንኦት ይሰጣሉ። ከንቲባዋ በተለይ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በምሳሌነት በመጥቀስ፣ "በፈረቃና በሌሊት የመሥራት ልምድ ፕሮጀክቶች ከተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ በፊት ጭምር እንዲጠናቀቁ ከማድረጉም በላይ፣ ጊዜን ወደ ኢኮኖሚያዊ ሀብት የመለወጥ ትልቅ አቅም መሆኑን በተግባር አሳይተናል" ይላሉ።

ይህ የሥራ ተነሳሽነት ለሕንፃዎች ግንባታ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ክብርና ምቾት የሚደረግ ጥረት መሆኑን የሚገልጹት ከንቲባዋ፣ በፈረቃ ሥራ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎችና የፕሮጀክቶች በፍጥነት መጠናቀቅ ተመልሰው ወደ ዜጎች ሕይወት የሚገቡ መሆናቸውን ጠቁመዋል።


ባለሙያዎች እንደሚተነትኑት፣ አዲስ አበባ የጀመረችው የ24/7 የሥራ ባህል በኢኮኖሚክስ ቋንቋ "የጊዜ ምርታማነት" (Time Productivity) ተብሎ የሚጠራውን ትልቅ ሀብት የመጠቀም ስልት ነው። የኮንስትራክሽን ዘርፍ አማካሪው ኢንጂነር ሰናይ ተካ እንደሚጠቁሙት፣ እንደ አዲስ አበባ ባሉ በፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ መዲናዎች ውስጥ ፕሮጀክቶችን በፈረቃ ማከናወን፣ የመሬትና የመሠረተ ልማት ዋጋ ሳይጨምር ምርታማነትን በሦስት እጥፍ ማሳደግ ማለት ነው።

እሳቸው እንደሚሉት ግንባታዎች በሌሊት እንዲከናወኑ ማድረጉ በቀን የሚታየውን የትራፊክ መጨናነቅ ከመቀነሱም በላይ፣ የማሽነሪዎችና የሰው ኃይል ሥራ ፈትተው የሚቀመጡበትን ጊዜ በማስቀረት የፕሮጀክቶችን ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል።

በሌላ በኩል፣ የሥነ ልቦና እና የማኅበራዊ ጥናት ባለሙያዋ ወይዘሮ ሰላማዊት ይመኙ ይህንን ለውጥ ከዜጎች የሥራ ተነሳሽነት ጋር ያገናኙታል። ሰዎች በሠሩት ሰዓትና በሰጡት ውጤት ልክ ክፍያ የሚያገኙበት ሥርዓት ሲዘረጋ፣ ሥራ ከልመናና ከጥገኝነት ወጥቶ የክብርና የብልጽግና ምንጭ ይሆናል ይላሉ።

ባለሙያዋ እንደሚገልጹት፣ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ተጠናቅቀው ለሕዝብ አገልግሎት ሲበቁ የሚፈጠረው የማኅበራዊ እርካታ ትርፍ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ፕሮጀክቶች በፍጥነት መጠናቀቃቸው ለነዋሪው ንጹሕ አየር፣ የእግር ጉዞ ስፍራ እና ቀልጣፋ ትራንስፖርት በቶሎ እንዲደርሰው ማድረጉ፣ በከተማዋ ነዋሪዎች ሥነ ልቦና ላይ "እኛም መሥራትና መለወጥ እንችላለን" የሚል ጠንካራ እምነትና የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር ማድረጉን በዋነኛነት ይጠቅሳሉ።

አዲስ አበባ አሁን የያዘችው የ7/24 የሥራ ባህልና የፈረቃ ልምምድ ከተማዋን ወደ ተሻለ ምዕራፍ የሚያሻግር ታላቅ የኢኮኖሚ ሞተር ነው። መዲናዋ እንደ አፍሪካ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷ፣ እንደ ኒው ዮርክ፣ ዱባይና ሴኡል ካሉ ዓለም አቀፍ ከተሞች ጋር በትከሻ ለመለካት የጊዜ አጠቃቀሟን ከዚህም የበለጠ ማዘመንና ሌሊቱን ወደ ሥራ ብርሃን መቀየር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።




ፎቶ- ከገፀ ድር

የአዲስ አበባ አዲስ የስራ ባህል ከተማዋን ቀንም ምሽትም የሚሰራባት አድርጓታል

# በአንድ ካርድ ብዙ ቁምነገር

- ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ነዋሪዎች ገልጸዋል

በስንታየሁ ምትኩ




የዘንድሮን ጨምሮ ባለፉት ጠቅላላ ምርጫዎች የምርጫ ካርድ የወሰዱ መራጮች ቁጥር

አቶ ጌታቸው ወልዴ ፒያሳ አካባቢ የሚኖሩ ሲሆን፣ ባለፉት ጊዜያት በተካሄዱት ጠቅላላ ምርጫዎች ሁሉ በንቃት ሲሳተፉ መቆየታቸውን ይገልጻሉ። በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫም የምርጫ ካርድ በመውሰድ፣ "ይበጀኛል" ለሚሉት የፖለቲካ ፓርቲ ድምፃቸውን ለመስጠት የድምፅ መስጫ ቀንን በጉጉት እየተጠባበቁ ይገኛሉ።

በምርጫው እየተፎካከሩ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎችና ክርክሮች በቴሌቭዥን መስኮት በንቃት በመከታተል በቂ መረጃ ማግኘታቸውን አቶ ጌታቸው ያነሳሉ። የዘንድሮው ምርጫ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እየተካሄደ መሆኑን፤ ሂደቱ በቀሪ ቀናትም ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ዜጎች ራሳቸውን በተለይም በማህበራዊ ሚዲያ ከሚሰራጩ የሀሰት መረጃዎች ማራቅ አለባቸው፡፡

የምርጫውን ውጤት በተመለከተም ማንኛውም ፓርቲ ቢያሸንፍ፣ ሕዝብ የሰጠውን ውሳኔ በጸጋ መቀበል እንደሚያስፈልግ አጽንኦት ሰጥተዋል። በተጨማሪም በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል አሸናፊና ተሸናፊ መኖሩን በማመን፤ ሁሉም ፓርቲዎች የምርጫውን ውጤት በሰላማዊና በበሰለ የፖለቲካ አስተሳሰብ ለመቀበል ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ሌላኛው የፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ ነዋሪ ወጣት ጌቱ በሽር፣ በዘንድሮው 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ የምርጫ ካርድ በማውጣት "ለሕዝብና ለአገር ሰላም እንዲሁም ዕድገት ይሠራል" ለሚለው የፖለቲካ ፓርቲ ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀቱን ይገልጻል። የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማኒፌስቷቸውንና የፖሊሲ አማራጮቻቸውን ሲያስተዋውቁ ሲከታተል መቆየቱን የሚያነሳው ወጣቱ፤ በዚህ መሠረትም በድምፅ መስጫው ዕለት "የበለጠ ይበጃል" ለሚለው ፓርቲ ድምፁን እንደሚሰጥ ተናግሯል።

ምርጫ፣ በሕዝብ አመኔታ ያገኘ ፓርቲ ወደ መንግሥት ሥልጣን በመምጣት አገር የሚያስተዳድርበት ሂደት ነው። ከዚህ አኳያ ዜጎች ያወጡትን የምርጫ ካርድ በዕለቱ ድምፅ በመስጠት ሊጠቀሙበት ይገባል። መንግሥት፣ ፓርቲዎችና የጸጥታ አካላት ከሁሉም በላይ ለሕዝብና ለአገር ቅድሚያ በመስጠት ሰላማዊ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ አለባቸው። መራጩ ሕዝብም ከምንም በላይ ሰላምን በማስቀደም መንቀሳቀስ አለበት። ለዚህም ከቤተሰብ ጀምሮ ሁሉም ሰው ኃላፊነት እንዳለበትና የምርጫው ሰላማዊ መሆን ለአገር የተሻለ ዕድል ይዞ እንደሚመጣም አስተያየቱን ሰጥቶናል፡፡

የአምስት ኪሎ ነዋሪዋ ወጣት ዮርዳኖስ ኤፍሬም፣ በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ድምፅ ለመስጠት የምርጫ ካርድ አውጥታ ዕለቱን እየተጠባበቀች ትገኛለች፡፡ በምርጫው 'ሕይወቴን ያሻሽልልኛል' ለምትለው የፖለቲካ ፓርቲ ድምፅ ለመስጠትም፣ የተለያዩ ፓርቲዎች የሚያደርጓቸውን ክርክሮች መከታተሏን ታነሳለች፡፡ ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆን በቤት፣ በሰፈርም ሆነ በየትኛውም አካባቢ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ የምታነሳው ወጣት ዮርዳኖስ፤ የምርጫው በሰላምና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መጠናቀቅ ከማንም በላይ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሴቶችን እንደሆነም ትገልጻለች።

> ሀገራችን የምትጸናውና ወደፊት የምትራመደው በዴሞክራሲያዊ ሂደት በድምፅ ስንወስን በመሆኑ መብታችንን በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል

በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ለሚፈልጉት አካል ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን የሚናገሩት ሌላኛው የገዳም ሰፈር ነዋሪ አቶ አከሊሉ ሽፈራው፤ ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ያነሳሉ። "ምርጫ ሲመጣ አንዳንድ ጊዜ ምን ይፈጠር ይሆን የሚል ሥጋትም አብሮ ይነሳል፤ ነገር ግን ሒደቱን በአግባቡና በሰላም ማከናወን ከተቻለ ለአገር ትልቅ ለውጥና ተስፋን ይዞ ይመጣል፤ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥትም ለሕዝብ ይሠራል" ይላሉ።

ሰላማዊ የምርጫ ባሕልን ለመገንባት እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት የሚገልጹት አቶ አከሊሉ፤ በምርጫ ወቅት ሁሉም ሰው ለአገሩ ዘብ መቆም እንዳለበትና ይህ ኃላፊነትም ከቤት መጀመር እንዳለበት ያሳስባሉ። "በዕድሜዬ ብዙ ነገሮችን አይቻለሁ" የሚሉት እኚሁ አባት፤ እያንዳንዱ ዜጋ በአካባቢው ሰላምን ካስከበረ፣ እንደ ከተማም ሆነ እንደ አገር አስተማማኝ ሰላም ማምጣትና አገርን ወደተሻለ ምዕራፍ ማሸጋገር እንደሚቻል ነው በልበ ሙሉነት የሚናገሩት፡፡

## የመራጮች ተሳትፎ ለሰላማዊ የምርጫ ባህል የሚኖረው ፋይዳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት መሠረት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ስድስት አጠቃላይ አገራዊ ምርጫዎችን አከናውኗል። በቦርዱ ገፀ ድር ላይ "ቀደምት ምርጫዎች" እና "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 6ኛው አጠቃላይ ምርጫ ውጤት" በሚል ርዕስ ሐምሌ 3 ቀን 2013 ዓ.ም የወጣው ሪፖርት እንደሚያሳየው፣ ከ1987 ዓ.ም እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በተካሄዱት ምርጫዎች የመራጮች ቁጥር በየጊዜው እያደገ መጥቷል።

በዚህ መሠረት በ1987 ዓ.ም ከተመዘገቡት ከ21 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ መራጮች ውስጥ 20 ሚሊዮኑ ድምፅ የሰጡ ሲሆን፣ በ1992 ዓ.ም ደግሞ ከተመዘገቡት ከ21 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ውስጥ 19 ነጥብ 6 ሚሊዮኑ ተሳትፈዋል። በ1997 ዓ.ም ከተመዘገቡት ከ27 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ዜጎች መካከል 22 ነጥብ 6 ሚሊዮኑ ድምፅ የሰጡ ሲሆን፣ በ2002 ዓ.ም ይህ ቁጥር አድጎ ከ31 ነጥብ 9 ሚሊዮን በላይ ከተመዘገቡት ውስጥ ደግሞ 29 ነጥብ 8 ሚሊዮኑ ምርጫው ላይ ተሳትፈዋል። በተመሳሳይ በ2007 ዓ.ም ከተመዘገቡት 36 ነጥብ 8 ሚሊዮን መራጮች መካከል 34 ነጥብ 3 ሚሊዮኑ ድምፅ የሰጡ ሲሆን፣ በ2013 ዓ.ም በተካሄደው 6ኛው አጠቃላይ ምርጫ ደግሞ ከ38 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ለመራጭነት ተመዝግበው በርካቶች ድምጽ ሰጥተዋል።

የ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ድምፅ የመስጠት ሂደት የፊታችን ሰኞ፤ ግንቦት 24 ቀን 2018 ዓ.ም ይካሄዳል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መረጃ እንደሚያሳየው በምርጫው 57 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሕዝብ በመራጭነት ተመዝግቧል። በየጊዜው የሚካሄዱ ምርጫዎች ለሰላማዊ የምርጫ ባሕል ግንባታ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው በመሆኑ፤ መራጩ ሕዝብ የወሰደውን የመራጭነት ካርድ በአግባቡ መጠቀምና ለምርጫው ሰላማዊነት የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ረዳት ፕሮፌሰር ያሬድ አያሌው (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ባለንበት ዘመን ዋነኛውና ተመራጩ የአስተዳደር ስርዓት የሕዝብ ሉዓላዊነት የሚረጋገጥበት የዴሞክራሲ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ምርጫ ሕዝብ በቀጥታ ተሳትፎ የሚያደርግበት፣ ተወካዮቹን ከወረዳ እስከ ፌዴራል ደረጃ የሚመርጥበት፣

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

ኢኮኖሚ

# ተረጂነትን የተፀየፉ እጆች

## “ተስፋ መቁረጥ እኔ ጋር አይታሰብም”

**የሴፍቲኔት ተጠቃሚ የነበሩ**

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ወይዘሮ ሰላም ሀብቱ ቱሉዲምቱ ዓለም ባንክ አካባቢ ነዋሪ ናቸው፡፡ በምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) መርሐ ግብር ታቅፈው ለሦስት ዓመታት ቆይተዋል። ወይዘሮዋን ያገኘናቸው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው በሚሠሩበት ቦታ ነው፡፡

“በመርሐ ግብሩ ታቅፈን ሥራ ከመጀመራችን በፊት የንግድ ክህሎት ሥልጠና ተሰጠን፡፡ በዚህም በምን ዘርፍ መሰማራት እንደምንፈልግ፣ ለምንሠራው ሥራ ምን ይዘን መነሳት እንዳለብን፤ በተጨማሪም ስለገንዘብ ወጪ፣ ገቢና አያያዝ ሥልጠና ወሰድን” በማለት በመርሐ ግብሩ ስላገኙት የንግድ ሥራ አጀማመር ሥልጠና ነግረውናል፡፡ በዚህ መሠረትም ከሚከፈላቸው ደመወዝ የቆጠቡትንና ድጋፍ የተደረገላቸውን ገንዘብ ተጠቅመው የፀጉር ቤት ዕቃዎችን በመግዛት የሴቶች የውበት ሳሎን እንደከፈቱ፣ በሥራቸውም ውጤታማ መሆናቸውንና የተበደሩትንም ገንዘብ በሦስት ወር ከፍለው እንደጨረሱ ይናገራሉ፡፡



ፎቶ-በገነት ወንድሙ
በሴፍቲኔት መርሃ ግብር መስሪያ ቦታ ተሰጥቷቸው በባልትና ውጤቶች እና በሴቶች የውበት ሳሎን ላይ የተሰማሩት ከግራ ወደ ቀኝ ወ/ሮ አዝመራ ጎበዜ እና ወ/ሮ ሰላም ሃብቱ

በምግብ ዋስትና መርሐ ግብሩ ታቅፈው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ኑሮን ለመምራት ተቸግረው እንደነበር በምሬት የሚያስታውሱት ወይዘሮዋ፤ “ልጅ የወለድኩት ካገባሁ ብዙም ሳልቆይ ነበር፤ ነገር ግን አራስ ቤት ተቀመጥኩ፡፡ ባለቤቴም የሚሠራው የቀን ሥራ በመሆኑ የሚገኘው ገቢ ቤተሰብ አያስተዳድርም፤ በዚህም ሕይወት ከባድ ሆነብኝ፡፡ እንኳንስ እንደ አራስ መታረስ ለዕለት በመቸገራችን፣ በተለይ እኔ ሕፃኗን በተገቢው ልክ ጡት ማጥባት አልቻልኩም ነበር” ሲሉ በሐዘን በመሞላታቸው ንግግራቸውን እንዲያቋርጡ አስገደዳቸው፡፡

በምግብ ዋስትና መርሐ ግብር መታቀፋቸው ከነበሩበት ከፍተኛ ችግር ከመውጣታቸው በተጨማሪ፣ በፊት የነበራቸው የሥራ ፍላጎት፣ ሥራና ሠራተኛ እንደተገናኘ ማሳያ መሆኑን ወይዘሮ ሰላም ለሥራ በተነሳሳና በጠነከረ አቅም ነግረውናል፡፡ “በአሁኑ ወቅት ፀጉር ከመሥራት በተጨማሪ የውበት ሳሎኔን ሙሉ ለማድረግ ጥረት እያደረግኩና ጥፍር መሥራትም ጀምሬያለሁ” ብለዋል። ሥራውን ውጤታማ ያደረገውና ለቤተሰቡም ጥሩ ገቢ ሊያስገኝ ያስቻለው በመርሐ ግብሩ ከድጋፉ በተጨማሪ በተዘጋጀው ሥልጠና አማካኝነት እንደሆነ፣ በፍላጎትና በእውቀት የተጀመረ ሥራ ውጤታማ እንደሚያደርግም አያይዘው ነግረውናል፡፡

“በመርሐ ግብሩ ያገኘሁት ድጋፍ አዲስ ሕይወት ለእኔም ሆነ ለቤተሰቤ አስገኝቶልናል፡፡ በተለይ የተሰጠኝ የመሥሪያ ቦታ ‘ቤት ኪራይ ምን ልክፈል?’ የሚል መሳቀቅ የሌለበት በመሆኑ እፎይታን ፈጥሮልኛል፡፡ ሠርቼ መቻሌንም ማሳያ ሆኖኛል” የሚሉት ወይዘሮ ሰላም፣ ወጥተው ሠርተው ሲገቡ አዕምሯቸው ዕረፍት እንደሚያገኝ ነው የነገሩን፡፡

“ተስፋ መቁረጥ እኔ ጋር አይታሰብም፤ ገበያ እንኳን ባይኖር ነገን አስባለሁ፤ ብወድቅ እነሳለሁ፤ ዛሬ ባጣ ነገ እንደማገኝ አምናለሁ” ሲሉ የወደፊት ሕልማቸው የሴቶች የውበት ሳሎን ማሠልጠኛ መክፈትና የዲኮር (ጌጣጌጥ) ሥራ መሥራት መሆኑን ነግረውናል፡፡

ሌላኛዋ በባልትና ውጤቶች ላይ ተሰማርተው ያገኘናቸው ወይዘሮ አዝመራ ጎበዜ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ከነበሩበት አስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ መላቀቅ መቻላቸውን ያነሳሉ፡፡ በምግብ ዋስትና መርሐ ግብር ከመታቀፋቸው በፊት ልጆቻቸውን ለማሳደግ በረንዳ ላይ ሻይና ቡና ይሠሩ እንደነበር ይገልጻሉ። እየሠሩም የቤት ኪራይ ክፍያ ሲያቅታቸው አከራዮቻቸው ቤት ውስጥ ባሉበት ሌሎች ተከራዮችን አምጥተው እንዳስወጧቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታቸው ነው፡፡

“በምግብ ዋስትናው መርሐ ግብር ከታቀፍኩ በኋላ በወር ሁለት ጊዜ የሕይወት ክህሎት ሥልጠና ይሰጠን ነበር፡፡ በመረጥኩት የንግድ ዘርፍ ዕቅድ እንዴት እንደሚታቀድ፣ ገንዘብና የደንበኞች አያያዝ ሥልጠና ወስጃለሁ። በወሰድኩት ሥልጠና መሠረትም ወደ ተግባር ገብቻለሁ” ሲሉ ወይዘሮዋ ነግረውናል፡፡

ወይዘሮዋ አያይዘውም የመንቀሳቀሻ ገንዘብ ድጋፍና የንግድ ክህሎቱ በመርሐ ግብሩ አማካኝነት መሰጠቱ የባልትና ውጤቶችን እንደ በርበሬ፣ ሚጥሚጣ፣ ሽሮ እና በሶ እያዘጋጁ በመሸጥ የቤተሰባቸው ኑሮ እየተሻሻለ መምጣቱን ነገሩን፡፡ በተለይም ከድጋፉ ጎን ለጎን የመሥሪያ ቦታ ማግኘታቸው ለለውጥ የበለጠ እንዳዘጋጃቸው ደስታ በፈነቀለው ስሜት ይናገራሉ፡፡

> “በአሁኑ ወቅት አድራሻ አለኝ። በኦንላይን ግብይት እየፈጸምኩ ነው። ወደ አውስትራሊያም አንድ ጊዜ ልኬያለሁ። መውደቅም መነሳትም እንዳለ ሆኖ፣ በተለይ ድጋፍ በሚያስፈልግ ወቅት ድጋፍ ካገኘ የሚሠራ የላቡን አያጣም፤ መንግሥትም ያደረገልን ድጋፍ በቀላሉ የሚታይ አይደለም

“በአሁኑ ወቅት አድራሻ አለኝ፡፡ በኦንላይን ግብይት እየፈጸምኩ ነው። ወደ አውስትራሊያም አንድ ጊዜ ልኬያለሁ። መውደቅም መነሳትም እንዳለ ሆኖ፣ በተለይ ድጋፍ በሚያስፈልግ ወቅት ድጋፍ ካገኘ የሚሠራ የላቡን አያጣም፤ መንግሥትም ያደረገልን ድጋፍ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በመርሐ ግብሩ ለታቀፍን ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻችን ትልቅ እገዛና ለውጥ ነው” ሲሉ ድጋፉ ያመጣላቸውን ለውጥ አያይዘው ገልጸውልናል፡፡ በዚህ ሥራም ከበፊቱ በተሻለ የሴቶች የቁጠባ ሒሳብ ከፍተው እንደሚቆጥቡና ልጆቻቸውን ማስተዳደር እንደቻሉም ይገልጻሉ፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የምግብ ዋስትና (ሴፍቲኔት) ቡድን መሪ የሆኑት አቶ ኤሊያስ ኢቲቻ ናቸው፡፡ በክፍለ ከተማው ዓለም ባንክ አካባቢ ለምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች G+4 ለማምረቻና መሸጫ አገልግሎት የመሥሪያ ሕንፃ ተገንብቶ አገልግሎት ላይ መዋሉን ያነሳሉ፡፡ በሕንፃው ውስጥ ሳሙና ማምረት፣ ልብስ ስፌት፣ ምግብ ዝግጅት፣ እንጀራ መጋገር፣ የሴቶች የውበት ሳሎን፣ የአትክልት ሽያጭ፣ የባልትና ውጤቶች፣ ጫማ ሥራ የመሳሰሉ ዘርፎች እንዳሉ ነግረውናል፡፡

ለእነዚህ ተጠቃሚዎች በየወረዳው አንዳንድ ባለሙያዎች ተመድበውላቸው ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ተጠቃሚዎች ቅዳሜና እሑድ ምርታቸውን ይዘው በየወረዳቸው የሰንበት ገበያዎች እንዲወጡ ይደረጋል። ለበዓልም ምርቶቻቸውን በባዛር አውጥተው እንዲሸጡ ይመቻችላቸዋል። በእንስሳት ተዋጽኦ ለተደራጁት ደግሞ ከቴክኒክና ሙያ ወተትና እንቁላል እንዲቀርቡላቸው የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ይህ ድጋፍና ክትትል ተጠቃሚዎቹ ሥራቸውን ወደውት እንዲሠሩና ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ነው ብለዋል አቶ ኤሊያስ፡፡ ተጠቃሚዎቹም ደስተኛ መሆናቸውን አያይዘው ገልጸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሥራና ክህሎት ቢሮ የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ተወካይና የሕብረተሰብ ተሳትፎ ቡድን መሪ አቶ አብርሃም እልፌ በበኩላቸው፤ ከተማችን አዲስ አበባ ለችግር የተጋለጡ ነዋሪዎችን ወደ ምርታማነት በማሸጋገር ረገድ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡ በዚህም መጋቢት 18 ቀን 2018 ዓ.ም የተመረቁትን በቤተሰብ ተወካይ 6 ሺህ 640፣ በቤተሰብ ሲታሰብ ደግሞ 19 ሺህ 20 የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህም በግንባታ፣ በከተማ

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የወንጀል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ምንድን ናቸው?

**መላኩ ተፈሪ ( ዐቃቤ ህግ )**

በወንጀል የፍርድ ሂደት ውስጥ ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ከመቃወሙ ወይም ጥፋተኛ ነኝ ወይም አይደለሁም ብሎ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት፣ በክሱ አመሰራረት ወይም በሕግ ረገድ ያሉ መሰረታዊ ክፍተቶችን በመጥቀስ መቃወሚያ የማቅረብ መብት አለው። እነዚህ መቃወሚያዎች "የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች" ተብለው የሚጠሩ ሲሆን፣ አላማቸውም የፍርድ ሂደቱን ፍትሃዊነት ማረጋገጥና አላስፈላጊ ክርክሮችን ለማስቀረት የሚረዳ ነው።

ተከሳሹ የክሱን ማመልከቻ ወይም ቻርጅ ወዲያውኑ ካልተቃወመ በቀር ቆይቶ እንዲህ ያለውን መቃወሚያ ነገሩ በሚሰማበት በሌላ ጊዜ ሊነሳ የሚችለው ፍርድ ቤቱን የሚፀና ፍርድ ለመስጠት የሚያግደው ከሆነ ብቻ ነው፤ በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130/3፡፡

ስለሆነም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ክሱ ከመሰማቱ በፊት መሆን እንዳለበት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ በግልፅ ያሰቀምጣል። ፍርድ ቤቱም የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ማስረጃ ሊሰማ ይችላል።



### ተከሳሹ ሊያቀርባቸው የሚችላቸው ዋና ዋና መቃዎሚያዎች

### 1. ክሱ በሌላ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ መሆኑ

ተከሳሹ የቀረበበት ክስ ቀደም ብሎ በሌላ የሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶ በመታየት ላይ ያለ ከሆነ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል።

### 2. ቀደም ሲል በዚሁ ክስ መታየትና ውሳኔ ማግኘት (Double Jeopardy)

ተከሳሹ በዚሁ ክስ ቀደም ሲል ለፍርድ ቀርቦ በነፃ የተለቀቀ ወይም ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ከሆነ በድጋሚ ሊከሰስ እንደማይችል በመጥቀስ መቃወም ይችላል።

### 3. ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑ (Statute of Limitation)

ወንጀሉ ከተፈጸመ በኋላ ክስ ለመመስረት በሕግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ ተከሳሹ ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን በመጥቀስ የመከራከር መብት አለው፡፡

### 4. ክሱ በምህረት ወይም በይቅርታ የሚታለፍ መሆኑ

የቀረበው የወንጀል ክስ በመንግሥት ምህረት (Amnesty) የተደረገበት ወይም ተከሳሹ በጉዳዩ ላይ ይቅርታ (Pardon) ያገኘ ከሆነ ክሱ ሊቀጥል የሚል መከራከር አይችልም።

### 5. የፍርድ ሂደቱ መከፋፈልን የሚጠይቅ መሆኑ

ተከሳሹ ከሌሎች ጋር አብሮ መከሰሱ የተከሳሹን የመከላከያ መብቱ ላይ ችግር የሚፈጥርበት ከሆነ ክሱ ተለይቶ እንዲታይለት የመጠየቅ መብት አለው።

### 6. ክስ ለመመስረት ሕጋዊ ፈቃድ አለማግኘት

አንዳንድ ወንጀሎች ክስ ከመመስረታቸው በፊት በሕግ ከተቀመጠ አካል ፈቃድ ማግኘትን የሚጠይቁ ሲሆን፣ ይህ ፈቃድ ሳይገኝ ክስ ከቀረበ ተከሳሹ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል። ለምሳሌ ተከሳሽ በዓለም አቀፍ ህግ ዲፕሎማቲክ ኢሙኒቲ የማይከሰስ እንደሆነ፣ አካለ መጠን ባልደረሱ ወጣት አጥፊዎች ላይ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ዐቃቤ ህግ ክስ ማቅረብ አይችልም።

### 7. የሌላ የፍርድ ሂደት ውሳኔን መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ

በወንጀል ክሱ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ሌላ የወንጀል ወይም የፍትሐ ብሔር ክርክር ውሳኔ ማግኘት የግድ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ክርክሩ እንዲቆይ መቃወሚያ ሊቀርብ ይችላል።

### 8. ተከሳሹ ለድርጊቱ ኃላፊነት የማይወስድ መሆኑ (Irresponsibility)

ተከሳሹ ለፈፀማቸው ተግባሮች ኃላፊ አለመሆን፤ ለምሳሌ የተከሳሽ እድሜ ከዘጠኝ ዓመት በታች ከሆነ፣ በወንጀል ህግ አንቀጽ 48 ላይ እንደተመለከተው ማንም ሰው በእድሜ፣ በህመም፣ ባልታሰበ የእድገት መዘግየት ወይም ጥልቅ በሆነ የአዕምሮ የመገንዘብ ችሎታ መቃወስ ወይም የወንጀል ድርጊት በሚፈፅምበት ጊዜ የድርጊቱን አይነት ወይም ውጤት ለመገንዘብ ወይም በዚህ ግንዛቤ መሰረት ራሱን ለመቆጣጠር በፍፁም ያልቻለ ሲሆን ኢ-ኃላፊ ስለሚሆን አይቀጣም፡፡

### 9. የቁስ ወይም የቦታ ሥልጣን የለውም

ተከሳሹ "ይህ ፍርድ ቤት ይህንን መዝገብ ለማየት የቁስ ወይም የቦታ ሥልጣን የለውም" የሚል የስልጣን መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል።

የቁስ ሥልጣን፡- ለምሳሌ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርብ። የቦታ ሥልጣን ደግሞ ወንጀሉ የተፈጸመበት ቦታ ከፍርድ ቤቱ የሥራ ክልል ውጪ ሲሆን።

### 10. የክሱ ግልጽ አለመሆን

ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገር እና ሁኔታዎች፤ ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ እና ስፍራ ተገቢ በሆነ ጊዜም በደል የደረሰበት ሰው ስም ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበት ንብረት፣ ተከሳሽ ድርጊቱን በመፈፀም የተላለፈው የህግ አንቀጽ መያዝ አለበት። ክሱ ግልፅ እና የተከሳሽን የመከላከል መብት የማያጣብብ መሆን አለበት፡፡

### 11. ሕጋዊ መሠረት ማጣት፡-

የተጠቀሰው ድርጊት በወንጀል ሕጉ ወይም በሌሎች ህጎች መሠረት ወንጀል ካልሆነ መቃወሚያ ማቅረብ ይቻላል ።

### 12 . የሕግ አጠቃቀስ ስህተት

በክሱ ላይ የተጠቀሰው የሕግ አንቀጽና የተገለጸው ድርጊት የማይገናኙ ሲሆኑ የቀረበውን ክስ መቃወም ይቻላል።

### 13. ክስ የመመስረት መብት መቃወሚያ

አንዳንድ ወንጀሎች (ለምሳሌ በግል አቤቱታ ክስ የሚቀርብባቸው) ክስ ለመመስረት የተለየ ሥነ ሥርዓት ወይም የግል ተበዳይ ፈቃድ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህ ካልተሟላ ተከሳሹ መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል።

የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ክሱ ከመሰማቱ በፊት መሆን እንዳለበት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ በግልፅ ያሰቀምጣል። ፍርድ ቤቱም የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ወዲያውኑ ውሳኔ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ማስረጃ ሊሰማ ይችላል

ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየወሩ የሚቀርብ

# ኮሌጁ በአዲስ ምዕራፍ

**በለይላ መሀመድ**


ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ባለፉት መቶ ዓመታት ለሀገርና ለዓለም የተረፉ በርካታ ምሁራንን፣ ፖለቲከኞችንና የጥበብ ሰዎችን አፍርቷል። ይህን የኢትዮጵያ የዘመናዊነት ታሪክ መነሻ፣ የቴክኖሎጂ እና የሀገሪቱ የብሩህ አዕምሮዎች መፈልፈያ የሆነውን ኮሌጅ የታሪክ ክብሩን አስጠብቆ ለመቀጠል አቅሙን ለማጠናከር በኮሌጁ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር ድጋፍ አንዱ ነው።

ወይዘሮ ቆንጂት ተድላ የቀድሞ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ተማሪ ነበሩ። ወደ ኮሌጁ ሊገቡ የቻሉት እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ውጤታቸው ከፍተኛ ስለነበር እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በ1962 ዓ.ም ወደ ኮሌጁ የገቡት ወይዘሮ ቆንጂት በሴክሬተሪያል ሳይንስ በከፍተኛ ማዕረግ መመረቃቸውን ያስታውሳሉ፡፡ በወቅቱ በኮሌጁ ይሰጡ የነበሩት የሙያ መስኮች ለሴት ሴክሬተሪያል ሳይንስ እና ባልትና (ሆም ኢኮኖሚክስ) ሲሆኑ ለወንዶች ደግሞ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ (አካውንቲንግ) እና ኢንዱስትሪያል አርት ነበሩ፡፡

ወይዘሮ ቆንጅት በአሁኑ ወቅት የማህበሩ የቦርድ ዋና ጸሐፊና የተማሪ ህብረቱ ዋና ተጠሪ ናቸው፡፡ ኮሌጁ ህይወታቸውንና ሙያቸውን የቀረጸ እንደሆነ ጠቅሰው አሁን ላይ የኮሌጁ አቅም ተጠናክሮ የቀደመ ትውልድ የመቅረጽ ተልዕኮውን በላቀ ደረጃ እንዲያሳካ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር በማቋቋም ድጋፍ የማድረግ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ነግረውናል፡፡

እንደሳቸው ገለጻ፤ እያደረጉት ካለው ድጋፍ መካከል የመጀመሪያ የቀድሞ ስሙን የማስመለስ ስራ መስራታቸውን ይናገራሉ፡፡ይህን ስሙን የማስመለስ ስራ አንዱ ታሪኩን የመጠበቅ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም የትምህርትና ስልጠና አቅሙን በማሳደግ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማህበሩ ሀብት በማፈላለግ የህንጻ ግንባታ እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተማሪ የስልጠና ጥራትን የሚያስጠብቅ በማህበሩ ኮሚቴ ማቋቋማቸውንም ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎች የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ በመስጠት፣ አቅም ለሌላቸው ሰልጣኞች ደግሞ የትምህርት እድል (ስኮላርሺፕ) በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል ኮሚቴው፡፡ እንዲሁም የትምህርት ቤቱን ታሪክ እና ሌሎች ትላልቅ አጀንዳዎችን ሰንዶ የያዘ እንደ ማጣቀሻ የሚያገለግልና በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቶ የሚጠናቀቅ መጽሐፍ ለማዘጋጀትም ጅምር ስራዎችን ኮሚቴው እየሰራ ይገኛል፡፡ በርካታ ታዋቂ ሰዎችን ያፈራው ኮሌጅ አሁንም የቀደመ ታሪኩን እንዲደግም የላቀ ደረጃ (School of Excellence) ላይ ለማድረስ በትጋት እየሰራ ነው ሲሉም ገልጸውልናል፡፡





ፎቶ- ከፋይል

በኮሌጁ ኢንተርፕራይዝ እየተመረቱ ካሉ ምርቶች መካከል የቆዳ ውጤቶች እና የእንስሳት መኖ ተጠቃሽ ናቸው

የዝግጅት ክፍሉ፤ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ከመንግስት ድጋፍ ወጥቶ ራሱን ለማብቃት እያደረገ ያለውን ጥረት አስመልክቶ የኮሌጁን ዲን አቶ ተሾመ ፈይሳን አነጋግሯቸዋል፡፡ እንደ ዲኑ ገለጻ፤ ኮሌጁ ካለው ታላቅ ታሪክ ተነስቶ የቴክኒክና ሙያ ዘርፎችን በማዘመን፣ የነገዎቹን የኢንዱስትሪ ባለቤቶችና ተፅዕኖ ፈጣሪ ዜጎችን የማፍራት ታሪካዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያደርገው ጥረት ከሚጠቀማቸው የገቢ ምንጮች መካከል አንዱ የመንግስት በጀት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኮሌጁ ከመንግስት በጀት ራሱን ለማላቀቅ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በግል እና በመንግስት አጋርነት የተለያዩ የፕሮጀክት ፈንዶችን በማፈላለግ ተቋሙ ያለበትን የቁሳቁስ፣ የገንዘብ ክፍተት በመሙላት ከመንግስት ጥገኝነት የሚላቀቅበትን አሰራር በመዘርጋት ላይ ነው፡፡

በግልና በመንግስት አጋርነት የተቋሙ የእግር ኳስ ሜዳ እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ ኮሌጁ የእግር ኳስ ሜዳውን በማከራየት ተጠቃሚ የሚሆንበት አሰራር ዘርግቷል። ሌላው በግልና በመንግስት አጋርነት በተቋሙ እየተሰራ ያለው በግቢው ችግኝ የማፍላት ስራ ነው፡፡ ችግኞቹን ለህብረተሰቡ በማድረስና በመትከል የአረንጓዴ ልማትን ለማስቀጠል እየሰራ ይገኛል፡፡

ሁለተኛው የኮሌጁ የገቢ አቅም ማሳደጊያ የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር (Alumni) ነው፡፡ ማህበሩ ሀብት በማፈላለግ የልማት ስራዎችን እየሰራ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በ70 ሚሊየን ብር ባለ ሶስት ወለል ህንጻ ግንባታ እየተካሄደ ነው፡፡ ይህ በቀድሞ ተማሪዎች ማህበር እየተሰራ ያለው ህንጻ ለመማሪያና ለመሰብሰቢያ የሚውል ሲሆን፤ ይህም ከመንግስት ይወጣ የነበረውን በጀት በመቆጠብ አበርክቶው ከፍተኛ ነው፡፡

> በግል እና በመንግስት አጋርነት የተለያዩ የፕሮጀክት ፈንዶችን በማፈላለግ ተቋሙ ያለበትን የቁሳቁስ፣ የገንዘብ ክፍተት በመሙላት ከመንግስት ጥገኝነት የሚላቀቅበትን አሰራር በመዘርጋት ላይ ነው

ከዚህ በተጨማሪም ኮሌጁ ከፕሮጀክቶች አቅሙን የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡ ፕሮጀክቶች ላይ የኢንቨስትመንት እቅድ በማስገባት ኮሌጁ ተጠቃሚ የሚሆንበት ስራ ይሰራል፡፡ በተለይም ከባለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ኮሌጁን በተሻለ ደረጃ የማደራጀትና የስልጠና ሂደቱን ሊያዘምኑ የሚችሉ ዲጂታል ስርዓት በመዘርጋት የተቋቋመበትን ዋና ተልዕኮ እውን ለማድረግ እየሰራ ነው፡፡ በፕሮጀክት ከ80 ሚሊየን ብር በላይ በሚሆን ወጪ በተቋሙ የኢንተርኔት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ተከናውኗል፡፡ በዚህ ገመድ አልባ ኢንተርኔት ማስገባት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአሰልጣኞችን አቅም የመገንባት እንዲሁም ምቹ የስልጠና አካባቢ ለመፍጠር ወርክሾፖችን የማደራጀትና እድሳት የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ወርክሾፖችና መጸዳጃ ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ ተሰርቷል። እነዚህ በፕሮጀክት የተሰሩ የልማት ስራዎች በተቋሙ አቅም ቢሰሩ 20 እና 30 ሚሊየን ብር የሚያስወጣ እንደሆነ የኮሌጁ ዲን ይገልጻሉ፡፡

የኮሌጁ ዲን አያይዘው እንደገለጹትም፤ በኮሌጁ የሚገኙ ኢንተፕራይዞችን ከማሰልጠን ባሻገር የውስጥ ገቢ ለማመንጨት የሚችሉበት አሰራርም ተዘርግቷል፡፡ ቀደም ሲል ኢንተርፕራይዞች የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ለህብረተሰቡ የማድረስ ስራ ከመስራት ባለፈ ህጋዊ እውቅናና ፍቃድ ስላልነበራቸው ስራዎችን እየተጫረቱ መስራት አይችሉም ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ህጋዊ እውቅናና ፍቃድ እንዲኖራቸው ተደርገው በመመስረታቸው ወይም የንግድ ፍቃድ በማውጣታቸው ከተቋማት ጋር ህጋዊ ደረሰኝ በመያዝ እንደማንኛውም ነጋዴ እየተጫረቱ ወደ ገበያ መግባት ይችላሉ፡፡ በኤስቴቲክስ ሙያ (ኪነጥበብ፣ ቴአትርና ሙዚቃ)፣ በአካባቢ ማስዋብ፣ በጋርመንት የተማሪዎች ልብስ ስፌት፣ በማኑፋክቸሪንግ የእንጨት ስራ ውጤቶች ማምረት፣ የጥገና ስራዎች፣ የማማከርና የሙዚቃ ባንድ ማቅረብ የመሳሰሉ ማምረትና አገልግሎቶች ላይ ከተቋማት ፍላጎት ሲቀርብ ኢንተርፕራይዞ እየተጫረተና ውል እየተዋዋለ የተቋሙን የገቢ አቅም ለማሳደግ የሚሰራበት እድል ተመቻችቷል፡፡ ዘርፉ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ከመንግስት በጀት ጥገኝነት ራሱን ለማላቀቅ ጠንካራ ስራ ለመስራት ቁርጠኛ አቋም መያዙም ነው የተጠቀሰው፡፡

እነዚህ በቀድሞ ተማሪዎች፣ በግልና በመንግስት አጋርነት፣ በፕሮጀክቶች እንዲሁም በኢንተርፕራይዞች እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ በቂ የማስተማሪያ ክፍል ለማግኘት ያስችላል። አሰልጣኞችን ለማብቃት ይረዳል፡፡ አይነ-ስውራንን ታሳቢ ተደርጎ የተሰራው መሰረተ ልማት ኮሌጁን ሁለገብና ምቹ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በኢንተርፕራይዝ የሚሰሩ ስራዎች ጠቀሜታቸው ገቢ ማስገኘት ብቻ ሳይሆን በሚመረቱ የኢንተርፕራይዝ ውጤቶች ሰልጣኞችና አሰልጣኞች የተግባር እውቀት እንዲኖራቸው እድል ያመቻቻል፡፡ የነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት የትምህርትና ስልጠና ጥራት ላይ ያለው አዎንታዊ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡


እንደ የኮሌጁ ዲን ገለጻ፤ ተቋሙ በሂደት ከመንግስት በጀት በመላቀቅ በራስ አቅም በጀቱን የሚሸፍንበትን አቅም ለመፍጠር እየሰራ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በዋናነት ኢንተርፕራይዞች በሙሉ አቅማቸው ወደ ገበያ እንዲገቡ ማድረግ ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የትምህርትና ስልጠና ጥራትን እውን ማድረግ ሲሆን ሰልጣኞችም በምርት ሂደቱ ራሳቸውን አካትተው ጥራት ያለው ምርት በማምረት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡

# ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች

**በጊዜው አማረ**


በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶችና አዳዲስ ጥበባዊ ሥራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ። ከተሰናዱት ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የመጻሕፍት ፊርማ፣ የሥነ-ጥበብ አውደ ርዕይ፣ የቴአትር መርሃ ግብርና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡










ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጻሕፍት

በዛሬው ዕለት መጽሐፍ የማስፈረምና የውይይት መርሃ ግብር ይካሄዳል። በቅርቡ "የጨረቃ ብርሃን" የተሰኘው የግለታሪክ መጽሐፍ በአድሃኖም ምትኩ እና በዮሐንስ አዝመራው ተዘጋጅቶ ለንባብ መብቃቱ ይታወቃል፡፡ ይህን ተከትሎ በዛሬው ዕለት ውይይት፣ የፊርማና የፎቶ መርሃ ግብር ከታሪኩ ባለቤት ከሆኑት ከወይዘሮ ብርሃኔ አስፋው ጋር ይደረጋል፡፡ መርሃ ግብሩ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት እስከ 10፡00 ሰዓት የሚቆይ ሲሆን፣ ቦታው ደግሞ ለገሃር ተወልደ ሕንጻ ሥር በሚገኘው ጃዕፈር መጻሕፍት መደብር ነው፡፡ ወይዘሮ ብርሃኔ ራሳቸው በመሠረቱትና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዕውቅና ባለው "ኢንተር-አፍሪካን ኮሚቴ" አማካኝነት ለ27 ዓመታት በ28 የአፍሪካ አገራት ውስጥ በተለይም የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም ያደረጉት ተከታታይ ንቅናቄ በመጽሐፉ ውስጥ በዝርዝር ተሰንዷል።

በሌላ መረጃ "የውቦች ንግሥት" የአጫጭር ልብ ወለድ መጽሐፍ ለቅድመ ሽያጭ ቀረበ፡፡ የደራሲት ምሕረት ደግፉ ሥራ የሆነው "የውቦች ንግሥት" አዲስ መጽሐፍ በሀገራችን እየተለመደ በመጣው የቅድመ ሽያጭ መርሃ ግብር ለሽያጭ የቀረበ ሲሆን፣ በቅርቡ ሕትመቱ ተጠናቅቆ አንባቢዎች እጅ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

## የሥዕል አውደ ርዕይ

"ስውር መልክ" የሥዕል አውደ ርዕይ ለእይታ በቃ፡፡ ስውር መልክ ወይም "ዘ ሂደን ፎርም" በተሰኘ መሪ ቃል የተዘጋጀው የሰዓሊ መሐሪ ተሾመ አውደ ርዕይ እስከ ሰኔ 7 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ ይቆያል። የሥዕል ማሳያ ቦታው ቦሌ ብራስ ኬኬር ሆቴል ሕንጻ ሁለተኛ ፎቅ ላይ የሚገኘው አርታዊ ጋለሪ ነው፡፡

እንዲሁም "ውብ አዲስ" የተሰኘው የሥዕል አውደ ርዕይ ነገ ከሰዓት ይጠናቀቃል፡፡ የሰዓሊ ሃሮን ሱሌይማን ሥራ የሆነው "ውብ አዲስ" የተሰኘው የሥዕል አውደ ርዕይ እየታየ የሚገኘው በጣይቱ የባህልና ትምህርት ማዕከል ነው።

በሌላ መረጃ ደግሞ "የዝምታ ወጎች" የሥዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል። ሰዓሊው ታሪኩ አስራት ሲሆን፣ አውደ ርዕዩ እየታየ የሚገኘው ኃያት ሪጄንሲ ሆቴል በሚገኘው የፊንድቃ ባህል ማዕከል ውስጥ ነው፡፡

## ሙዚቃ

የድምጻዊት ሰላማዊት ዮሐንስ አዲስ ሙዚቃ ትናንት ምሽት ተለቀቀ። በበርካታ ተወዳጅ ነጠላ ሙዚቃዎቿ የምትታወቀው ሰላማዊት፣ አሁን ደግሞ "መን" የተሰኘውን ሥራዋን በናሆም ሪከርድስ አማካኝነት ወደ አድማጭ ተመልካች አድርሳለች፡፡ ድምፃዊት ሰላማዊት ዮሐንስ ሚዛን፣ ሰናይ፣ ሃምበል፣ ሃነን፣ ዞማዋ፣ ምላስ፣ ናፍቆትና ሌሎችንም ተወዳጅ ነጠላ ዜማዎች ወደ ሕዝብ ማድረሷ ይታወቃል፡፡

## የቴአትር መርሃ ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሑድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። ቅዳሜ "12ቱ እንግዶች" ቴአትር በ8፡00 ሰዓት እና በ12፡00 ሰዓት ይታያል። እሑድ በ7፡30 ሰዓት "ንጉሥ አርማህ" ቴአትር፣ እንዲሁም "እምዬ ብረቷ" የተሰኘው ቴአትር በ11፡30 ሰዓት ላይ ይታያሉ። በብሔራዊ ቴአትር ለሚታዩ ቴአትሮች ተመልካቾች ጊዜያቸውን ለመቆጠብ "ሁሉ በጄ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል። በተጨማሪም "ባልቻ አባነፍሶ" ቴአትር እሑድ በ8:00 ሰዓት በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የሚታይ ሲሆን፣ ትኬት በኢንተርኔት (ኦንላይን) የክፍያ ሥርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተገልጿል።

በሀገር ፍቅር ቴአትር ደግሞ "ነገሩ አይቆምም" ሐሙስ በ11፡30 ሰዓት፣ "ሰዴታ" (በአፋን ኦሮሞ) እሑድ በ8፡00 ሰዓት እንዲሁም "የመጨረሻው ፍርድ" እሑድ በ12፡00 ሰዓት ለቴአትር አፍቃሪያን ይታያል፡፡ በተጨማሪም "አዮ ቦራ" የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ የሕጻናት ቴአትር ቅዳሜ ጠዋት በ4፡00 ሰዓት በሕጻናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ለእይታ ይቀርባል፡፡ በተመሳሳይ "የሰማይ ልጆች" የተሰኘው ቴአትር እሑድ ጠዋት ከ4፡00 ሰዓት ጀምሮ ፍላሚንጎ በሚገኘው በሕጻናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ይታያል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ


## የባለፈው ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በእያንዳንዱ ባለ አራት ጎን ውስጥ የሚገኙ ቁጥሮች ድምር 25 መሆን አለበት። በዚህ አምክንዮ መሰረት የመጀመሪያው 6 + 3 + 5 + 8 + 3 = 25 ይሆናል፡፡ ሁለተኛው 8 + 2 + 1 + 7 + 7 = 25 ነው፡፡ በዚህ መሰረት የመጨረሻው 5 + 1 + 6 + 9+4 = 25 ይሆናል። ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር **4** ነው፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል። በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# በሚሊዮኖች ስክሪን ላይ የበራችው ኢትዮጵያ




ፎቶ-ከገፀ ድር
ኢትዮጵያን የጐበኙ ታዋቂ ቲክቶከሮች በከፊል

**በአብርሃም ገብሬ**

ፈጣን በሆነው የመረጃ ዘመን የዓለምን የቱሪዝም ገበያ መሪነት መያዝም ሆነ የሀገራትን ገጽታ የመገንባት ሂደት ላይ ፈጣን ለውጥ እየታየ ነው፡፡ በነባሩ የመገናኛ ዘዴ ከሚጠይቀው የብሮድካስት ማስታወቂያ ዘዴዎች ወጣ በማለት፣ ወደ ስማርት ስልኮቻችን ስክሪኖች እየተዘዋወረ ይገኛል። ከዓመታት በፊት የቱሪስቶች መዳረሻነት የሚወሰነው በትላልቅ ሚዲያዎች በሚሰሩ ዘጋቢ ፊልሞች፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች ቢሆንም፣ በዚህ ዘመን ግን ይህ አካሄድ እየተለወጠ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ በሚሊዮኖች ዘንድ ተዓማኒነት ያላቸው የማህበራዊ ሚዲያ የይዘት ፈጣሪዎች የሀገራትን ባህል፣ ታሪክ፣ ዕድገትና መልካም ገጽታ በማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተወጡ ናቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተለመዱ የፖለቲካ ዜናዎች ይልቅ በመዝናኛና በዲጂታል የትስስር ገጾች ላይ "ሰበር ዜና" የነበረውና የዓለምን ትኩረት በከፍተኛ ሁኔታ ስበው የነበሩ ኩነቶች በኢትዮጵያ እየተስተዋሉ ነው፡፡ የዓለም አቀፍ ዲጂታል ሚዲያ ኮከቦችና የይዘት ጉዳይ ተጽዕኖ ፈጣሪዎችም ኢትዮጵያን እየጎበኙ መሆናቸውን ተከተሎ ነው፤ ኢትዮጵያና አዲስ አበባ በስፋት እየተጠሩ ያሉት፡፡ የተጽዕኖ ፈጣሪዎቹ የኢትዮጵያ ጉብኝትም፣ በተለይ የቱሪዝም ዘርፍ ትርክትና ገጽታ በዲጂታሉ ዓለም እንዴት እንደተቀየረ የሚያስረዳ ጥሩ ማሳያ ነው። ይህ ክስተት የሀገሪቱን ገጽታ በቀጥታ ስርጭት ጭምር ለዓለም ያሳየ በመሆኑ፣ በቱሪዝም ማስተዋወቅ ረገድ አዲስ ምዕራፍ ከፋች ሆኗል።

## ታዋቂ የይዘት ፈጣሪዎች ጉብኝት በኢትዮጵያ

ባሳለፍነው ሳምንት በሚሊዮኖች ተከታዮች ያሉትና በማኅበራዊ ትስስር ገጾች ዓለም "የዜና አባት" (News Daddy) በሚል መጠሪያው የሚታወቀው ታዋቂው ብሪታንያዊ ጋዜጠኛ ዴላን ፔጅ (Dylan Page) ኢትዮጵያን ተዘዋውሮ ጎብኝቷል፡፡ ከእሱ በፊት በዩቲዩብ ብቻ ከ54 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች ያሉት አሜሪካዊው ወጣት አይሾ ስፒድን (IShowSpeed) ጨምሮ የአፍሪካ የይዘት ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል። በተለይ ዴላን ፔጅና አይሾ ስፒድ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በ"ምድረ ቀደምት" ኢትዮጵያ ያደረጉትን ታሪካዊ ጉብኝት ለበርካታ ሚሊዮን ተከታዮቻቸው አስተላልፈዋል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት የኢትዮጵያ ጉብኝቱን አጠናቅቆ ወደ ሀገሩ የተመለሰው ዴላን ፔጅ 19 ነጥብ 6 ሚሊዮን ተከታዮች ባሉት የቲክቶክ ገጹ እያንዳንዱን ጉብኝቱን በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ ተከታዮቹ አጋርቷል፡፡ ዴላን ፔጅ በቲክቶክ፣ በፌስቡክና በዩቲዩብ ገጾቹ የኢትዮጵያን ጉብኝቱን አጠናቅቆ ወደ ሀገሩ ሲመለስ በቪዲዮ መልዕክት አጋርቶ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ አስደናቂ ሀገር መሆኗ፣ በተመለከታቸው ነገሮች እጅግ መደሰቱ፣ ወደ ሀገሩ ከሄደ በኋላም ኢትዮጵያ እንደምትናፍቀውና ተመልሶ ኢትዮጵያን እንደሚጎበኝ ተናግሯል፡፡ "በህይወቴ እንዲህ አይነት አስደናቂ የህይወት ልምድ ኖሮኝ አያውቅም፡፡ በጣም አስደሳችና ተናፋቂ ጊዜ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፍኩት፡፡ እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ተመልሼ ወደ ኢትዮጵያ እመጣለሁ" በማለት ነበር፤ በዓለም ዙሪያ ለሚገኙ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ተከታዮቹ መልዕክት ያጋራው፡፡

ዴላን ፔጅ ስለ ኢትዮጵያ የሰራቸው ቪዲዮዎች በብዙ ሚሊዮን ታይተዋል። ዴላን ፔጅ አዲስ አበባን ተዘዋውሮ ጎብኝቷል፡፡ በከተማዋ ውበትም ተደምሟል፡፡ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትና ታሪካዊቷ የሀረር ከተማን ጎብኝቷል። ዴላን ፔጅ በተለይ በሀረር ጉብኝቱ ወቅት፣ በአፍ በተያዘ እንጨት ጅቦችን ሲመግብ የሚያሳየው አስገራሚ ቪዲዮ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን አስደምሟል።

> **በሚሊዮን የሚቆጠሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን አመለካከት የቀየረ ታላቅ የዲጂታል ዲፕሎማሲ ስራ ነው። የእነዚህ ሰዎች ይዘቶች "Addis Ababa" እና "Ethiopia" የሚሉትን ቃላት በዓለም አቀፍ የዲጂታል ሚዲያ የፍለጋ ድሮች (ሰርች ማድረጊያዎች) ላይ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያደረገ ነው**

ይህ በሀረር የታየው ትዕይንት በሰው ልጅና በዱር እንስሳት መካከል ያለውን አስደናቂ ተስማምቶ የመኖር ጥበብ እንዲሁም የሀረርን ህዝብ እንግዶችን በክብር የመቀበል ልዩ ባህል ለዓለም ማህበረሰብ በጉልህ ያስተዋወቀ ነው። የቪዲዮው ይዘት በአጭር ጊዜ ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ፍጥነት መታየቱን ተከትሎ፣ ብዙዎች በትዕይንቱ ተገርመው አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

## የታዋቂ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉብኝት እና የቱሪዝም መነቃቃት

"የዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች የኢትዮጵያ ጉብኝት በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ምን አይነት ፋይዳ ይኖረዋል?" ሲል የዝግጅት ክፍላችን አንጋፋው የቱሪዝም ጉዳዮች ከፍተኛ ተመራማሪና አማካሪ የሆኑትን አያሌው ሲሳይ(ዶ/ር)ን ጠይቋል። እንደ አያሌው (ዶ/ር) ገለጻ፣ ቀደም ሲል የነበረው ባህላዊ የቱሪስት መስህቦችን የማስተዋወቅ ዘዴ ውስብስብና ወጪ የሚጠይቅ እንደነበር ያስታውሳሉ። "በቀደመው ጊዜ ለማስተዋወቅ መጽሔት፣ ጋዜጣ፣ ሲዲ፣ ዲቪዲ ሳይቀር ተሸክመን ነበር የምንሄደው፡፡ አሁን እሱ ቀርቷል" የሚሉት ተመራማሪው፣ የዲጂታላይዜሽኑ መስፋፋት ይህንን እንግልት ከማስቀረቱም በላይ የአካባቢ ብክለትን(Environmental Pollution) ለመቀነስ ጭምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉን ተናግረዋል።

ይህ በቴክኖሎጂ የታገዘ አዲስ አቀራረብ ቱሪስቶች ካሉበት ሆነው መረጃዎችን በቀላሉ እንዲያገኙ ትልቅ በር ከፍቷል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ተጓዦች ወደ አንድ ሀገር ለመሄድ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት ዲጂታል አማራጮችን እንደሚፈትሹ ምሁሩ ይገልጻሉ። ታዋቂ የይዘት ፈጣሪዎችና ጋዜጠኞች እያዩት ያለውን ትዕይንት በቀጥታ ለሚሊዮን ተከታዮቻቸው ያሰራጫሉ፡፡ በዚህ የቀጥታ ስርጭት ወቅት በዓለም ዙሪያ ያሉ በርካታ ግለሰቦች ከቤታቸው ቁጭ ብለው መከታተል ይችላሉ፡፡ ይሄ አጋጣሚ ደግሞ በተዘዋዋሪ የዚያን ሀገር የቱሪዝም ሀብቶች፣ የባህልና የመዝናኛ አማራጮችን የማስተዋወቅ ዕድል እንደሚፈጥር ተናግረዋል፡፡

አያሌው(ዶ/ር) አክለውም፤ የይዘት ፈጣሪዎች ወደ አዲስ አበባና ወደተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ተዘዋውረው መጎብኘታቸው በቱሪዝም መነቃቃት ላይ የራሱ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የዲጂታል ሚዲያ ተጠቃሚው በበዛበት በዚህ ዘመን የተመልካችን ትኩረት ስቦ ለማቆየትና ወደ ተግባር ለመለወጥ ተከታታይነት ያለው የክትትል ስራ ይጠይቃል፡፡ ኢትዮጵያ ካሏት የቱሪስት መስህቦች በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ ምቹ የትራንስፖርት አማራጮች መኖራቸውን እግረ መንገድ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ እንደ ዴላን ፔጅ እና አይሾ ስፒድ ያሉ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉብኝት ወደ ዘላቂ የቱሪስት ፍሰት መቀየር እንደሚቻልም ነው አያሌው (ዶ/ር) የተናገሩት፡፡

ታዋቂው የይዘት ፈጣሪና ዘጋቢ ዴላን ፔጅ በአዲስ አበባ በነበረው ቆይታ የከተማዋን ታሪካዊና ዘመናዊ ገጽታዎች ጎን ለጎን ለዓለም አስተዋውቋል። በአዲስ አበባ የዓድዋ ድል መታሰቢያን የጎበኘ ሲሆን፣ የከተማዋን አዳዲስ የልማት እና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶችን (የኮሪደር ልማትን) በመዘዋወር በቅርበት ተመልክቷል። ይህም አዲስ አበባ ጥንታዊ ታሪኳንና የአፍሪካ መዲናነቷን ጠብቃ፣ ዘመናዊነቷንና ለቱሪስቶች ያላትን ምቾት እያፋጠነች ያለች ማራኪ የቱሪስት መዳረሻ መሆኗን በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ተመልካቾች በቪዲዮ ቀርጾ አስተላልፏል።

የእነዚህ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉብኝት ስለ ሀገሪቱ ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ስለ

ወደ ገጽ 16 ዞሯል

ከአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# የማህበሩ የለውጥ ምስጢር ምንድን ነው?

**• ስትራቴጂክ ዕቅዱ ማህበሩን ከልማዳዊ አሰራር አውጥቶ ተቋማዊ አቅምን በማጠናከር የአባላቱን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ መሆኑ ተገልጿል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**



ፎቶ፡- ከፋይል

በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ አማካኝነት ለአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማህበር በተዘጋጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ ስልጠና ሲሰጥ

የአመራር አካዳሚዎች በአንድ አገር ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግንባታ ውስጥ ያላቸው ሚና ተቋማዊ ስኬትን ከማረጋገጥ ባለፈ፣ አሳታፊ እና ስልታዊ የሆኑ ግቦችን በመቅረፅ ረገድ የማይተካ ሚና አላቸው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታዩ ስኬታማ ተሞክሮዎች እንደሚያመለክቱት፣ እነዚህ አካዳሚዎች የአመራር ክህሎትን ከዘመኑ ቴክኖሎጂ እና ስትራቴጂያዊ አስተሳሰብ ጋር በማጣመር የተቋማትን የአፈፃፀም አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግራል።

ይህ የተቋማት ስኬት ሚስጥር ደግሞ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ባካተተ መልኩ ሲተገበር ይበልጥ ትርጉም ያገኛል። በተለይም በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ ለሚሰሩ ተቋማት የአመራር አካዳሚዎች የሚኖራቸው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነው። አካል ጉዳተኝነትን ከበጎ አድራጎት ባለፈ በሰብዓዊ መብት እና በልማት እይታ የሚመሩ አመራሮችን በማፍራት፣ ተቋማቱ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆነ የስራ አካባቢ እንዲፈጥሩ እና ስትራቴጂያዊ ግቦቻቸው አካታች እንዲሆኑ ያስችላሉ።

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የአመራር ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል። የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበርም አንዱ የዚህ ዕድል ተጠቃሚ ነው፡፡ ማህበሩ ከነበረበት ውስንነቶች ወጥቶ ጠንካራ፣ ተደማጭ እና ለአባላቱ የሚተርፍ እንዲሆን የሚያስችለውን አቅም እንዲያፈራ ከአመራር አካዳሚው ሙያዊ ድጋፎችን አግኝቷል፡፡ ማህበሩ ከቀድሞው የዘፈቀደ አሰራር ወጥቶ በታቀደ መልኩ መስራት የሚያስችለው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ እና ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን አግኝቷል።

ማህበሩ ከአመራር አካዳሚው ያገኛቸው ስልጠናዎች እንዲሁም የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተቋማዊ አቅምን ለመገንባት፣ የፋይናንስ አቅምን ለማጠናከር፣ የአባላትን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ብሎም ግንባር ቀደም የአመራር ሚና እንዲኖረው በዕቅድ የመመራት ዕድልን እንዳጎናፀፈው ከሁለቱም ተቋማት የስራ ኃላፊዎች ያገኘናቸው መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ለአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ያዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማህበሩ ካለበት ተቋማዊ ድክመት ወጥቶ የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችለው ወሳኝ ፍኖተ ካርታ መሆኑን በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት ከፍተኛ አማካሪ ሰላም ተወልደብርሃን ገልፀዋል፡፡

አካዳሚው ለአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ያዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የተዘጋጀበት ዋና ዓላማ በቀደመው ጊዜ ከወረዳ እስከ ከተማ (ማዕከል) ድረስ ወጥ አሰራር ባለመኖሩ ነው ብለው፣ አሰራሩ ከላይ እስከታች ወጥነት እንዲኖረው ወይም የተቀናጀ እንዲሆን እቅዱ በብርቱ እያገዘ ነው ብለዋል፡፡

በአማካሪዋ ማብራሪያ መሠረት፣ አካዳሚው ስትራቴጂክ እቅዱን ካዘጋጀ በኋላም ዝም ብሎ አልተዋቸውም። ዕቅዱን በተመለከተ ከከተማ እስከ ክፍለ ከተማ ደረጃ ላሉ አመራሮች ስልጠና ሰጥቷል፤ ስልጠናው መስማት ለተሳናቸው በምልክት ቋንቋ እንዲደርስ ተደርጓል፤ ይህም አካታች እንዲሆን ያስችለዋል፡፡ ዕቅዱ ዐይነ ስውራንንም ታሳቢ አድርጎ በብሬል ተዘጋጅቶ ለከተማ እና ለአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ተደራሽ ተደርጓል፡፡

ለማህበሩ የተዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ከ2016 እስከ 2020 ዓ.ም የሚተገበር ሲሆን፣ ማህበሩ ለረጅም ዓመታት ሲከተለው የነበረው አሰራር በዘመናዊ የአመራር ጥበብ ያልተደገፈ በመሆኑ ለበርካታ ውስብስብ ችግሮች ተጋልጦ መቆየቱን በአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማህበር የቦርድ አባልና የሂሳብ ሹም አቶ ለገሰ ኃይለማርያም ገልፀዋል። ጉዳዩን ሲያብራሩም፣ በአመራር አካዳሚው አማካኝነት የተዘጋጀው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ግልጽ የሆነ አሰራርን ለመዘርጋት በማስቻሉ የአሰራር መሻሻሎችን በማስገኘት ላይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አቶ ለገሰ በማብራሪያቸው፣ የአካል ጉዳተኞች በከተማዋ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ይህንን ለመቀየር የሚያስችል ስልታዊ አቅጣጫ ለመንደፍም ስትራቴጂክ ዕቅዱ ያግዛል፡፡ ስትራቴጂክ ዕቅዱ የተዘጋጀው ከመንግስት ፖሊሲዎች ጋር መጣጣም፣ ማህበሩ ከከተማ አስተዳደሩና ከሀገራዊ የዕድገት ግቦች ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ የሚያስችል የጋራ ራዕይ ለመፍጠርም ጭምር እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

ስትራቴጂክ ዕቅዱ ከመዘጋጀቱ በፊት የአካል ጉዳተኛ ማህበራት ወጥ የሆነ አሰራር እንዳልነበራቸው፣ ሁሉም በየራሳቸው መንገድ ከመንቀሳቀሳቸውም በላይ ሪፖርት የሚያደርጉበት መንገድም የተዘበራረቀ እንደነበር፤ በመዋጮ አሰባሰብ ረገድም ሆነ የአባላት ምልመላቸው የተዘበራረቀ እንደነበር፣ ስትራቴጂክ ዕቅዱ ደግሞ የተናበበና ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖራቸው ማድረጉ ተገልጿል፡፡

የውሳኔ አሰጣጥ ጥራትን በማሻሻል የየማህበራቱ አመራሮች በዘፈቀደ ሳይሆን በመረጃና በጥናት ላይ ተመስርተው ውሳኔዎችን እንዲያስተላልፉ ስትራቴጂክ ዕቅዱ መሰረት ከመጣሉም ሌላ ተከታታይነት ያለው ክትትልና ግምገማ ለማድረግም የላቀ አበርክቶ አለው። የተከናወኑ ስራዎችን ለመለካት የሚያስችሉ ቁልፍ የውጤት አመላካቾች ስላለው፣ ስራዎች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅና ማስተካከያ ለማድረግ ማገዙንም አቶ ለገሰ ተናግረዋል፡፡

በአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት ከፍተኛ አማካሪ ሰላም ተወልደብርሃን ስትራቴጂክ ዕቅዱ የተፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ አካዳሚው በምን አግባብ ይከታተላል? ብለን ላነሳንላቸው ጥያቄ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በማብራሪያቸውም፣ አካዳሚው የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን እቅዱን እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉና ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለባቸውም ጭምር ስልጠና መስጠቱን ጠቁመዋል፡፡

አካዳሚው ዕቅዱን ማዘጋጀቱ በራሱ ማህበሩ ከልማዳዊ አሰራር ወጥቶ ወደ ውጤት ተኮር ስርዓት እንዲሸጋገር ያደረገ ትልቅ መሠረት መሆኑን አንስተው፣ ስኬታማነቱ ግን በዋናነት የሚወሰነው በዕቅዱ ጥራት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በአመራሩ ቁርጠኝነትና በባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ላይ እንደሆነ አብራርተው፣ ስኬታማ መሆን በሚችልበት ልክ መደገፉ ግን እንደቀጠለ ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር የቦርድ አባልና የሂሳብ ሹም አቶ ለገሰ ኃይለማርያም በመንግስትም ሆነ በግል ተቋም ስራዎችን በተፈለገው ጊዜና ጥራት ለማከናወን ስትራቴጂክ ዕቅዱ የጎላ አስተዋፅኦ እያበረከተ እንዳለ ጠቁመው፣ ከከተማ እስከ ክፍለ ከተማ እና ወረዳ ድረስ ያሉ አመራሮች ስራቸውን ወጥ በሆነ መንገድ በስኬት እንዲመሩ እድል የሰጠ ትልቅ ግብዓት እንደሆነ መስክረዋል፡፡

እንደ አቶ ለገሰ፣ በ2016 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ማህበሩ ሪፎርም ማድረጉን ገልፀው፣ በዚህም ማህበሩ አካል ጉዳተኞችን በአግባቡ ያላካተተ፣ የሴቶችንም የመሪነት ሚና ከግምት ያላስገባ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ማህበሩ ለረጅም ዓመታት ሲከተለው የነበረው አሰራር በዘመናዊ የአመራር ጥበብ ያልተደገፈና ወጥነት የሚጎድለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስትራቴጂክ ዕቅዱ ደግሞ እነዚህን ክፍተቶች በሚታይ መልኩ እየሞላ ይገኛል፡፡

የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ግልጽ በሆነ ስትራቴጂክ ዕቅድ መመራታቸው ተልዕኳቸውንና ራዕያቸውን በውል ለይተው እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። ዕቅዱ ማህበሩ ካለው ውስን ሀብትና የሰው ኃይል አንጻር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት እንዲለይ፣ የገቢ ምንጮቹን እንዲያሰፋና የአባላቱን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በዘላቂነት እንዲያረጋግጥ ይረዳዋል።

አንድ ማህበር ለረጅም ዓመታት ያለ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሲንቀሳቀስ ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣል። ዋነኛው ጉዳት የተቋሙ ጉዞ በዘፈቀደና በወቅታዊ ኩነቶች ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ የሀብት ብክነትን ያስከትላል፣ ተቋማዊ ተጠያቂነትን ያጠፋል፣ እንዲሁም ማህበሩ ለውጫዊ ለውጦችና ተግዳሮቶች በቀላሉ እንዲሸነፍ ያደርገዋል። ግልጽ አቅጣጫ በሌለበት ሁኔታ የአባላት ፍላጎት በአግባቡ ስለማይመለስ፣ ማህበሩ በሂደት ተሰሚነቱና ጥንካሬው እየቀነሰ እንዲሄድ ያደርገዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ከበርካታ ዓመታት በኋላ አሁን የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ነድፎ ወደ ተግባር መግባቱ ትልቅ የተቋማዊ ዕድገት ማሳያ ነው። ይህ እርምጃ ማህበሩ ካለፈው የአሰራር ልምድ ወጥቶ ወደ ዘመናዊና ውጤት ተኮር አመራር መሸጋገሩን ያረጋግጣል። ዕቅዱ በቀጣዮቹ ዓመታት የሚሰሩ ስራዎችን በዝርዝር የያዘ በመሆኑ፣ የአባላቱን መብት ለማስከበርና ማህበራዊ ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት በተደራጀ መንገድ ለመምራት ያስችላል። ይህም ማህበሩ በከተማዋ ውስጥ ካሉ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሲቪክ ማህበራት ተርታ እንዲሰለፍ እድል ይፈጥርለታል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ሞሰብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# አዳዲስ አገልግሎቶችን አካትቶ የመጣው ማዕከል

• አዲስ የተካተቱት የከተማ አስተዳደሩ የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲሁም ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ተቋማት ናቸው

**በደረጀ ታደሰ**

አቶ ሲሳይ እንዳለ ይባላሉ። ነዋሪነታቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ነው፡፡ ግለሰቡን ያገኘናቸው በክፍለ ከተማው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ማዕከል ከመጀመሪያዎቹ ተገልጋዮች መካከል አንዱ ሆነው በተገኙበት ወቅት ነበር፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ 7ኛው ሆኖ ለአገልግሎት በበቃው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማዕከል የመጡበትን ምክንያት እና ከተቋሙ ጋር በተያያዘ የታዘቡትን አስተያየት እንደሚከተለው አጋርተውናል፡፡ “ወደ ማዕከሉ የመጣሁት የመንጃ ፈቃድ ለማደስ ነው፡፡ መጀመሪያ ሐሳቤ ከዚህ በፊት ወደማውቀው ተቋም በማምራት ለማደስ ነበር፡፡ ነገር ግን ጓደኛዬ ማዕከሉ እዚህ አቅራቢያችን እንደተከፈተ በሰጠኝ መረጃ መሠረት ወደዚህ መጣሁ፡፡ 30 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፣ በጥሩ መስተንግዶ፣ የመንጃ ፈቃዴ ታድሶ እጄ ላይ ገብቷል፡፡"

የመንጃ ፈቃዳቸውን የመታደሻ ጊዜ ማለፉን ያወቁት ወደ ማዕከሉ ከመምጣታቸው አንድ ቀን ቀደም ብሎ መሆኑን ያስታወሱት ተገልጋዩ፤ ከጓደኛቸው መረጃውን ባይሰሙ ኖሮ ቀደም ሲል መሰል አገልግሎቶችን ወደሚያገኙበት፣ ለእርሳቸው ቅርብ ወደሆነውና በተለምዶ አርሴማ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ካለው የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ተቋም በማምራት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የአገልግሎቱን ተደራሽነት በፍጥነት እያሳደገ የመጣው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት በ7ኛው ማዕከሉ አቅራቢያቸው በመገኘቱ፣ ከመንጃ ፈቃድ ማደስ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ ጨርሶ ለመውጣት ወደ ማዕከሉ ገቡ፤ ያሰቡትንም አገኙ፡፡ ይህ ሁኔታም ከዚህ በፊት ይሄዱበት የነበረውን ተቋም እና የአዲስ መሶብን አገልግሎት ልዩነት በተጨባጭ ለመግለፅ ያስቻላቸው ሲሆን፤ “ነባሩ ተቋም ተገልጋይ ይበዛዋል፡፡ ከበሩ ጀምሮ ‘ማነህ፣ የትነህ፣ ወዴትነህ?' የሚል ወከባ ይበዛዋል። በማዕከሉ ግን በወከባ ሳይሆን በጣም የተረጋጋ፣ ሥርዓት ያለው፣ ጥሩ አቀባበልና መስተንግዶ የሚታይበት ነው፡፡ መጣሁ፣ ገባሁ፣ ጉዳዬን ጠየቁኝ፣ መረጃ ተሰጠኝ፣ በሚመለከተው ክፍል ተስተናገጄ፣ ጨርሼ ወጣሁ” በማለት ልዩነቱን አብራርተዋል፡፡

በከተማ አስተዳደር ደረጃ አገልግሎታቸውን በአዲስ መሶብ አማካኝነት እያቀረቡ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡ ይህ ተቋም በአዲስ መሶብ ማዕከል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ (የመንጃ ፈቃድ) እድሳትን ጨምሮ 11 የሚሆኑ አገልግሎቶችን ያቀርባል:::




ፎቶ፡- ከፋይል

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ማዕከል ውጫዊ ገጽታ

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን ለህብረተሰቡ ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ፣ አዲስ በተገነባ ባለ 6 ወለል ሕንጻ፣ በቴክኖሎጂና በግብዓት በተደራጀ ተቋም ሥራውን ስለመጀመሩ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በይፋዊ የማህበራዊ ሚዲያ ትስስር ገጻቸው ላይ መልዕክት አስተላልፈው ነበር፡፡ ባስተላለፉት መልዕክትም፤ ለዘመናት በተንዛዛ አሠራርና እጅ መንሻ እየተጠየቀበት ዜጎችን ሲያማርር የነበረውን የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ችግር ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ መፍታት መቻሉን አስፍረዋል፡፡

አገልግሎት አሰጣጡንም ቀልጣፋ፣ የዘመነ እና ፍትሐዊ ለማድረግ 'አንድ' ተብሎ የተጀመረውን የመሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ለማህበረሰባችን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ በተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎትም መስጠት መጀመሩን አንስተዋል፡፡

በተመሳሳይ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማዕከል ለአገልግሎት በበቃበት ወቅት ባደረጉት ንግግር፤ ከዚህ በፊት ሲተገበሩ የነበሩ የመንግሥት አገልግሎት ማሻሻያዎች ቀላል የማይባል ውጤት ቢያመጡም፣ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ላይ ግን ጉድለት እንደነበረባቸው ያስታወሱት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ፤ ይህንን የተመለከቱት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የመሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት እንደ አገር እንዲጀመር ሐሳብ አመንጭተው፣ እንዲተገበር አመራር መስጠታቸውንና አሁን ላይ ለሚታየው ውጤት ትልቁን አስተዋፅኦ ማበርከታቸውን እያይዘው ገልጸዋል፡፡

እንደ አገር የተቀመጠውን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን አመራር መነሻ በማድረግ፣ የመሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎትን አዲስ አበባ በግንባር ቀደምትነት በመጀመር እና በፍጥነት ተደራሽነቱን በማስፋት ምሳሌ የሚሆን አፈፃፀም እያሳየች መሆኑን ምክትል ከንቲባው አቶ ጃንጥራር አስረድተዋል፡፡ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋ እና የተገልጋዩን እርካታ ከፍ እንዲል የመሶብ አገልግሎት ወሳኝ መሆኑን በመጠቆም፤ ይህ የተቋም ግንባታ ሥራ ትኩረት እንዲሰጠው ካደረጉ ምክንያቶች መካከል በኢኮኖሚ ስርጭት ላይ ያለው ሚና ትልቅነት አንዱ መሆኑን ጠቁመዋል። "የመንግስት አገልግሎትን ማዘመንና ማሻሻል፣ የመንግስት ገቢን ያሻሽላል፤ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የሚከናወኑ ሥራዎችን ይደግፋል፤ የጊዜና የሀብት ብክነትን ይቀንሳል" ብለዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተደራሽነት ማደግ፤ በሕዝብ ላይ ከአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር የሚፈጠሩ ቅሬታዎች እና ምሬቶችን፣ በተቋማት ላይ የሚታዩ የሙስናና የሌብነት ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓትን ለመዘርጋት እንደሚጠቅም አቶ ጃንጥራር አብራርተዋል፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ተገንብቶ ለአገልግሎት የበቃው 7ኛው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ከዚህ ቀደም ለአገልግሎት ከበቁ ማዕከላት የሕንጻ ዲዛይንን ጨምሮ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ መቅረቡ ልዩ እንደሚያደርገውም ገልፀዋል፡፡ ማዕከሉ የቤት ለቤት እና የቪአይፒ (VIP) አገልግሎቶችን ለመስጠት የተዘጋጀ ስለመሆኑም አንስተዋል፡፡

ወይዘሮ ትዕግስት ሚሊዮን የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ ሥራ አስኪያጇ አዲሱን ማዕከል በብቃት ወደ ሥራ ለማስገባት ከሕንጻው ቅጥር ግቢ ጀምሮ በእያንዳንዱ ወለል ላይ በመንቀሳቀስ የአመራርነት ሚናቸውን ሲወጡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በፊት የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ቦሌ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሲያገለግሉ መቆየታቸውና ያካበቱት ልምድ ለአዲሱ ማዕከል ስኬታማነት እንደሚያግዛቸው ይታመናል።

ሥራአስኪያጇ ስለማዕከሉ የአገልግሎት አጀማመር፣ ተቋማዊ አደረጃጀቱ እና ዝግጁነቱን በተመለከተ ለዝግጅት ክፍላችን ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡ እሳቸው በሰጡን ማብራሪያ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ማዕከል ከዚህ ቀደም ለአገልግሎት ከበቁት የአዲስ መሶብ ማዕከላት አንጻር ልዩ የሚያደርገው ነገር አለው፡፡ ከልዩ መገለጫዎቹ መካከል ለተገልጋይ የሚያቀርባቸው አገልግሎቶችና የተቋማት ቁጥር መጨመሩ አንዱ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በነበሩት ማዕከላት የ20 ተቋማትን 117 አገልግሎቶች በመያዝ ሲሆን፤ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ማዕከል ግን በ22 ተቋማት 119 አገልግሎቶችን በማካተት ነው ሥራውን በይፋ የጀመረው፡፡ በማዕከሉ እንደ አዲስ የተካተቱት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ተቋማት አገልግሎቶች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የማዕከሉ ሕንጻ ከዲዛይን ጀምሮ፣ የቦታ መረጣ፣ ስፋትና ምቹነት ላይ በጣም ታስቦበት የተሠራ በመሆኑ ከሌሎቹ የተለየ እንደሚያደርገው አስረድተዋል፡፡ አሁን ላይ በሕብረተሰቡ ዘንድ ስለ አዲስ መሶብ አገልግሎት ያለው ግንዛቤ እየተሻሻለ መምጣቱን ተከትሎ፤ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተገልጋዮች ማዕከሉ ሥራውን ከጀመረበት ዕለት አንስቶ ለአገልግሎት እንዲመጡ እንዳገዛቸውም አልሸሸጉም፡፡

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገኝ ሲሆን፤ ሥራውን የጀመረው የአራዳ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የቀድሞ ሕንጻን በማደስ እና በማዘመን እንደሆነ ይታወቃል። ከዚህ በኋላ ለአገልግሎት ከበቁት አምስት ማዕከላት መካከል አብዛኞቹ ነባር ሕንጻዎችን በማደስ ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን፤ የሚገኙበትም አካባቢ ከክፍለ ከተሞች የአስተዳደር ሕንጻ አቅራቢያ ነው፡፡ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ማዕከል ግን ከእነዚህ በተለየ መልኩ ከክፍለ ከተማው አስተዳደር ሕንጻ መገኛ ራቅ ብሎ ነው፡፡ የአዲስ መሶብ ንፋስ ስልክ ማዕከል መገኛ አድራሻ፣ በተለምዶ “ቫርኔሎ” አደባባይ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው፡፡ ከዋና መንገድ ተዋስኖ የተገነባው ማዕከሉ፣ የመሶብ ቅርጽ ባለው የሕንጻ ዲዛይን መገንባቱ ለማንኛውም ሰው በቀላሉ ለመለየት ያስችለዋል፡፡

የመንግስት አገልግሎቶችን በጥራት፣ በፍጥነት፣ ጊዜና ወጪን በሚቆጥብ እና የተገልጋይን እርካታ በሚያሻሽል መልኩ ማቅረብን ዓላማ በማድረግ ተደራሽነቱን እያሳደገ የመጣው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት፣ ጷጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም. ሥራውን 'አንድ' ብሎ በይፋ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ግንቦት ወር አጋማሽ ድረስ ከ200 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት መስጠቱን የተቋሙ መረጃ ያመለክታል፡፡ የተገልጋዮቹ የአገልግሎት እርካታ ደረጃም ከ98 ከመቶ በላይ ደርሷል፡፡

ከቀናት በፊት (ግንቦት 19 ቀን 2018 ዓ.ም.) ለአገልግሎት በበቃው 7ኛ ማዕከሉም መሰል አገልግሎቶችን እያቀረበ ይገኛል። በዚህ ማዕከልም በአቅራቢያው የሚገኙ እንዲሁም በተለያየ አጋጣሚ ወደ አካባቢው የሚመጡ የከተማዋ ነዋሪዎች ከቀረቡላቸው 119 አገልግሎቶች መካከል የሚፈልጉትን ማግኘት ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት አማራጭም ከደጃቸው የሚመጣውን አገልግሎት መጠቀም የዜግነት መብታቸው ነው፡፡ ስለሆነም በፍጥነት እየዘመነች፣ እየተመቸች፣ እየተዋበችና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቷ እያደገ ከመጣችው አዲስ አበባ የበለጠ ለመጠቀም እንደ ነዋሪ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ የከተማ አስተዳደሩ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

የዜግነት መብታቸው ነው፡፡ ስለሆነም፤ በፍጥነት እየዘመነች፣ እየተመቸች፣ እየተዋበችና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቷ እያደገ ከመጣችው አዲስ አበባ የበለጠ ለመጠቀም እንደነዋሪ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ከተማ አስተዳደሩ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

# ልጆች፤ ክህሎታችሁን እንዴት እያዳበራችሁ ነው?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? ዛሬ ከመደበኛው መማር ማስተማር በተጨማሪ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን የሰሩ ልጆች እናስተዋውቃችኋለን። እናንተስ ምን አይነት ችሎታ ነው ያላችሁ? እንዴትስ እያዳበራችሁት ነው?

ዮሴፍ ዋለልኝ እባላለሁ፡፡ እድሜዬ 16 ነው፡፡ የምማረው በገላን የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ያለ ሰው ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ የሚችል ተሽከርካሪ የፈጠራ ስራ ሰርቻለሁ፡፡ የወሰደብኝ ጊዜም ሁለት ወር ነው፡፡

ይህ የፈጠራ ስራ የሚሰጠው ጥቅም የአንድ አካባቢ የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ ሁኔታ ይጠቁማል፡፡ የእሳት አደጋ ቢከሰት አደጋው በስንት ሰዓት እንደተከሰተ፣ የት ቦታ እንደሆነ የአካባቢውን ፎቶ በቀጥታ ይልክለታል። በተገጠመለት ጂፒኤስ ዳሰሳ በማድረግ አንድ ሰው አንድ ቦታ ሆኖ መኪናውን ወደፈለገበት ቦታ የትራፊክ ፍሰቱን ጠብቆ እንዲሄድ ያደርጋል። በተጨማሪም መልክአምድራዊ አቀማመጥ፣ ከባህር ወለል በላይ ያለውን ከፍታ፣ አጠቃላይ የአየር ንብረቱን ሁኔታም መረጃ መስጠት የሚያስችል ነው፡፡

በዚህ የፈጠራ ስራዬም የሜዳሊያ ሽልማት አግኝቻለሁ፡፡ የእውቅና የምስክር ወረቀትም ተሰጥቶኛል፡፡ ስለ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃ የሚሰጥ መጽሐፍም ተሰጥቶኛል፡፡ ይህ እውቅና ህልሜን እውን የሚያደርግልኝ ነው፡፡

የሰራሁት የፈጠራ ስራ "እኔም እችላለሁ" የሚል በራስ መተማመንን በሌሎች ላይ ይፈጥራል፡፡ እነሱም ለስራ ፈጠራ እንዲበረታቱ ይረዳቸዋል፡፡ ለችግሮች መፍትሄ መፈለግ እንዳለባቸው እንዲረዱ ያግዛቸዋል፡፡ ለፈጠራ ሲነሳሱ በአካባቢያቸው ያሉ ችግሮችን እንዲያስተውሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ለችግሮች መፍትሄ እንዳላቸው ይማሩበታል፡፡ እኔም በዚህ መንገድ ነው የፈጠራ ስራዬን የሰራሁት፡፡


ፎቶ፡- ገነት ወንድሙ
በግራ በኩል የሚገኘው ዮሴፍ ዋለልኝ የፈጠራ ሥራውን ለእይታ ባቀረበበት ወቅት

በረከት በትሩ እባላለሁ፡፡ የምማረው ሃና ቅድመ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን የ7ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ ሰዎች ተጠቅመው የጣሏቸውን ነገሮች ለእኔ ጥቅም አላቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ተጠቅመው የጣሏቸውን ቁሶች መግጠምና መፍታት እንዲሁም መመራመር ደስ ይለኛል፡፡ ቤት ውስጥ እቃ ሲበላሽም እፈላሰፍበታለሁ፡፡

የ4ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ልጆች በሃይላንድ "መኪና ነው" እያሉ በመሬት ላይ አንዱ ተቀምጦ አንዱን በገመድ እየሳበው በመንሸራተት ልብሳቸውን ሲያቆሽሹና ሲቀዳደድ እመለከት ነበር፡፡ በዚህ መሰረት እኛ ልጆች ባለንበት ሆነን በሪሞት (እንቅስቃሴ በመቆጣጠሪያ) የምትንቀሳቀስ መኪና ሰርቻለሁ። በካርቶን የተሰራች ብትሆንም ዲናሞ የተገጠመላት፣ መሪ፣ ጎማና የውስጥ አካላት የተሟሉላት ናት፡፡ ወደፊትም ትልቅ መኪና መስራት እንደምችል ተምሬበታለሁ፡፡

ሌላኛው በ11ኛው ከተማ አቀፍ የሳይንስ ፈጠራ ስራ አውደ ርዕይ ላይ ይዤው ቀርቤ የነበረው የፈጠራ ስራዬ የሎተሪ እድል ተጠቃሚነትን የሚያሰፋ ነው። የፈጠራ ስራውን የጀመርኩት 3ኛ ክፍል እያለሁ ነበር፡፡ ስራው ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ ባለበት 5ኛ ክፍል ስደርስ ሂሳብ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ርዕሰ ጉዳዩን አገኘሁት። ከዚያም እንደገና ለመስራት ተነሳሳሁ። አላማውም አንድ ሰው ከአንድ ጊዜ በላይ የሎተሪ እጣ በመሞከር የሎተሪ እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ነው።

የፈጠራ ስራዬን የሰራሁት ከወዳደቁ እቃዎች ሲሆን፤ እነዚህም አራት ማዕዘን ያለው ጣውላ፣ ዲናሞ፣ ስምንት ከለር የተለያዩ የእጣ ስሞች ያሉበት ወረቀት፣ ማብሪያና ማጥፊያ ናቸው። በኤሌክትሪክ ቻርጅ የተደረገው ባትሪ ሲያልቅበት ከፀሐይ ብርሃን ሃይል በመሰብሰብ ይሰራል፡፡ ዲናሞው ሲሽከረከር ከስምንቱ እድሎች ውስጥ በአንዱ ላይ ያመለክታል። ይህ ማለትም አንድ ሰው በተደጋጋሚ ስምንት እድሎችን መጠቀም የሚችልበት ነው፡፡

ጓደኞቼም ከእኔ የፈጠራ ስራ ሊማሩ የሚገባቸው ማንኛውም የተጣለ ነገር ቆሻሻ ሳይሆን ከተጠቀምንበት ዋጋ አለው። አዕምሯችንን እንዲሰራ ማድረግ መቻል አለብን፡፡ ሁላችንም የተደበቀ ተሰጥኦ አለን ይህንን ተሰጥኦዋችንን በመሞከር ልናወጣው ይገባል፡፡

## ተአምረኛው የጥጥ ፍሬና እጀ ወርቆቹ ሸማኔዎች!




ውድ ህጻናት፣ ዛሬ በምድራችን ላይ ስላለው አንድ አስደናቂና ውብ ጥበብ ላውጋችሁ! በእርሻ ውስጥ የምታዩት ለስላሳውና ነጩ የጥጥ ፍሬ፣ በእናቶቻችን እንዝርት እየተፈተለ ወደ ቀጭን ክር ይለወጣል። ከዚያም ታታሪ እጀ ወርቆቹ መወርወሪያቸውን እንደ ወፍ እያበረሩ፣ እጃቸውንና እግራቸውን በቅኝት እያንቀሳቀሱ ክሮቹን እርስ በርስ ያቆራኟቸዋል።

ይህ በሰው እጅ የሚሰራው ድንቅ የሸማ ጥበብ የሀገራችን የኢትዮጵያ ትልቅ ኩራት ነው! አንድ ነጠላ ክር በቀላሉ ቢበጠስም፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ክሮች በአንድነት ሲሸመኑ ግን ብርድን የሚከላከል ጠንካራ ጋቢና ማራኪ ቀሚስ ይሆናሉ። ይህ ታሪክ እኛም በአንድነትና በፍቅር ከቆምን የማይበገሩ ጀግኖች እንደምንሆን ያስተምረናል።

የኢትዮጵያ የሸማ ልብስ ሙሉ በሙሉ ከተፈጥሮ ጥጥ ስለሚሰራ በበጋ ወቅት ያቀዘቅዛል፣ በክረምት ደግሞ እጅግ ሞቅ ያለ እቅፍ ይሰጣል!

በበዓላት ቀን በቀለማት ያሸበረቀውን የሸማ ልብሳችንን ለብሰን ስንወጣ፣ ውበታችን ልክ እንደ ቀስተ-ደመና ያበራል። ታዲያ ልጆች፣ የሀገራችንን ባህል በመልበስና በማክበር ይህንን ድንቅ የእጅ ጥበብ ለዘላለም እናስቀጥለው!

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሆዷን ሞልታ ሌላውን በሆዷ ሰክታ**

**መልስ፡-** ሊ. ጃርት

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**አንዲት ግንድ በሁለት ትከሻ ትጓደድ**

ሀ. ኩንታል
ለ. እንስራ
ሐ. ቀንበር

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ከእርሻ የፈለቁ የኢንቨስትመንት ምንጮች

- **55 የቀድሞ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ተቀላቅለው ስኬታማ መሆናቸው ተጠቁሟል**



ፎቶ- ከፋይል
አርሶ አደር ተስፋዬ ደገፋ በተሽከርካሪ አካላት ማምረቻ ማዕከላቸው ውስጥ



ፎቶ- ከፋይል
አርሶ አደር ለገሰ ገላና ከተሰማሩባቸው የኢንቨስትመንት ስራዎች አንዱ የሆነው የበሬዎች ማድለቢያ ነው

በይግለጡ ጓዴ

አርሶ አደር ለገሰ ገላና በተለምዶ ሰሚት ተብሎ በሚጠራው የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ነዋሪ ናቸው፡፡ ጥቂት ዓመታትን የኋሊት ህይወታቸውን ሲያስታውሱ እዝነ ልቦናቸው በትዝታ ይሞላል። "በፊት በዚህ አካባቢ ስንዴና ጤፍ አምርቼ፣ ከተዋጣላቸው የሀገሬ ገበሬዎች እኩል ሞዴል ተብዬ የተሸለምኩ ጠንካራ አርሶ አደር ነበርኩ" ይላሉ። ይሁን እንጂ የከተማዋን መስፋፋት ተከትሎ ያ ምርት የሚያፍሱበት የሚያመርቱበት ሰፊ ማሳ በልማት ምክንያት ተወሰደ። ያኔ ህይወት በአንድ ጀምበር ተቀየረች። መሬት መሄድ ብቻ አልነበረም፤ ከእሱ ጋር የማህበራዊ ትስስር ገመድ መበጠስ፣ የኢኮኖሚ ዋስትና ማጣትና ከባድ የስነ-ልቦና ስብራት ተከተለ። ልክ እንደ እርሳቸው ሁሉ በአዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩ በርካታ አርሶ አደሮች መሬታቸው ያለ በቂ ካሳና ያላግባብ በካሬ ሜትር በትንሽ ብር እየተሰላ ሲወሰድባቸው፣ የከተማዋ እድገት ለእነርሱ የበረከት ሳይሆን የጭንቀት ምንጭ ሆኖ ሰንብቷል።

ነገር ግን ታሪክ ሁልጊዜ ባለበት አይረግጥም፤ ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ የመንግስት እይታና አቅጣጫ መለወጥ ጀመረ። "የከተማ መስፋፋት አርሶ አደሩን ማፈናቀል የለበትም፤ ይልቁንም የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ ማድረግ አለበት" የሚል አዲስ እይታ ተፈጠረ፤ ይህንን ተከትሎ አርሶ አደር ለገሰ የይዞታ መሬታቸው ተከብሮላቸው፣ ህጋዊ ካርታ በእጃቸው ገባ። ያኔ ነው እንግዲህ በትናንቱ የእርሻ ማሳቸው ላይ አዲስ የኢንቨስትመንት ስራ የጀመሩት።

አርሶ አደር ለገሰ አሁን በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት በመገንባት በትውልድ ላይ ሀብታቸውን እየዘሩ ይገኛሉ። ትምህርት ቤታቸው ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያስተምራል። ከዚህም ባሻገር በተቀናጀ የከተማ ግብርና ዘርፍ በመሰማራት በከብት ማድለብ፣ በወተትና በዶሮ እርባታ ውጤታማ መሆን ችለዋል። ትናንት መሬታቸውን አጥተው የሰው እጅ ያዩ የነበሩት አርሶ አደር፣ ዛሬ በከተማ ግብርና ለሰባት ወጣቶች ቋሚ የስራ ዕድል የፈጠሩ ታላቅ ባለሃብት ሆነዋል።

ይህ አዲስ የተስፋ ጭላንጭል በለሚ ኩራ ብቻ ያበቃ አይደለም፤ ወደ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ስናመራም ሌላ አስደናቂ ታሪክ እንሰማለን። በአያት ቅድመ አያቶቻቸው ዘመን ጀምሮ ሲያርሱት በነበረው መሬት ትርፍ ምርት ያመርቱ የነበሩት አርሶ አደር ተስፋዬ ደገፋ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ መሬታቸው በልማት ተወስዶባቸው ለከፋ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ተጋልጠው ነበር። "ያኔ መሬታችን በካሬ በአነስተኛ ዋጋ፣ አንዳንዴም ምንም ካሳ ሳይሰጠን ይወሰድብን ነበር፤ አርሶ አደሩ ለከፋ መከራ ተጋልጦ ነበር" ሲሉ ያንን ጊዜ ያስታውሳሉ።

ነገር ግን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲጂታል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ሲሰጣቸውና ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ መንገዱን ሲያሳያቸው አርሶ አደር ተስፋዬ ፈተናውን ወደ ዕድል ቀየሩት። አሁን ላይ ለተቀናጀ የከተማ ግብርና ስራ የሚሆን ዘመናዊ ሁለገብ መጋዘን እየገነቡ ከመሆኑም በላይ፣ ወደ ከባድ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተሻግረዋል። አቶ ዮሴፍ ገብረኪዳን ከተባሉ አጋራቸው ጋር በሽርክና በመቀናጀት፣ በብረታ ብረት ስራ የነዳጅ ቦቴ እና ተሳቢ የሎቤድ መኪናዎችን የመገጣጠም ስራ ውስጥም ገብተዋል።

የአርሶ አደር ተስፋዬና የአቶ ዮሴፍ ተቋም አሁን ላይ የደረቅ ጭነት ማመላለሻዎችን፣ የነዳጅ ማመላለሻ ቦቴዎችንና የማደያ ታንከሮችን እያመረተ ይገኛል። ይህ ተቋም ለ88 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር ችሏል። አጋራቸው አቶ ዮሴፍ እንደሚሉት፣ መንግስት በመስሪያ ቦታና በፋይናንስ ብድር በኩል ድጋፉን አጠናክሮ ከቀጠለ፣ ከውጭ የሚገቡ የከባድ መኪና መገጣጠሚያ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ በማስቀረት ሀገሪቱን ከተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ወጪ ማዳን ይቻላል። ትናንት ለማህበራዊ ችግር ተጋልጠው የነበሩት አርሶ አደር ዛሬ ህይወታቸው ተቀይሮ አምራችና የሀገር ባለውለታ ሆነዋል።

እነዚህ ስኬቶች በዘፈቀደ የመጡ ሳይሆኑ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ስር በተቀረጹ ስልታዊ አሰራሮችና መመሪያዎች የተገኙ ናቸው። የኮሚሽኑ የአርሶ አደር ልማት ቡድን መሪ ወይዘሮ ደግነሽ በደዊ እንደሚሉት፣ ከዚህ ቀደም አርሶ አደሩ መብቱ ተከብሮለት አያውቅም ነበር። ነገር ግን ከለውጡ ወዲህ መመሪያ 20/2013 በመዘጋጀቱ፣ አርሶ አደሩ በራሱ ይዞታ ላይ ቅድሚያ አግኝቶ እንዲያለማ ህጋዊ መሰረት ተጥሏል።

ባለፉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ወደ ኢንቨስትመንት ለመግባት ፍላጎት ያላቸውና የተለዩ አርሶ አደሮች ቁጥር 2 ሺህ 470 መድረሱን የኮሚሽኑ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከእነዚህ ውስጥ፣ 190 አርሶ አደሮች ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ሁኔታዎች ተመቻችቶላቸው ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል። 60 አርሶ አደሮች ፕሮጀክታቸው ሙሉ በሙሉ የፀደቀላቸው ሲሆን፣ የቀሩት 130 አርሶ አደሮች በከንቲባ ጽሕፈት ቤት፣ በፕላን ልማት ቢሮ እና በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በኩል በማመቻቸት ሂደት ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ ወደ ኢንቨስትመንት በቀጥታ ከገቡት አርሶ አደሮች መካከል 10ሩ በኮሚሽኑ የተመቻቸላቸው ሲሆን፣ 45ቱ በራሳቸው ጥረት ገብተው፣ በአጠቃላይ 55 አርሶ አደሮች በኢንቨስትመንት ዓለም ውስጥ ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ 35 አርሶ አደሮች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች (በትምህርት ቤት፣ በጤና፣ በመኖ ማቀነባበር፣ በግብርና ልማትና በማኑፋክቸሪንግ) ተሰማርተው ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ "ሞዴል አርሶ አደሮች" ለመሆን በቅተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮች አሁን ላይ ሌላው ያገኙት ትልቅ ዕድል ከገበያው መቃረባቸው ነው። ቀደም ሲል ያመረቱትን ምርት በርካሽ ዋጋ ከእነሱ ተቀብለው ሸማቹን በውድ ዋጋ ይበዘብዙ የነበሩ ደላላዎችን በማስቀረት፣ ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለሸማቾች ማህበራት፣ ለትላልቅ ሆቴሎችና ለሱፐርማርኬቶች ማቅረብ ጀምረዋል። ይህም ለአርሶ አደሮች የተሻለ ትርፍ፣ ለከተማዋ ነዋሪ ደግሞ ትኩስና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የምግብ አቅርቦት እንዲኖር አድርጓል። በማድለብ፣ በወተት ልማትና በዶሮ እርባታ የተሰማሩት አርሶ አደሮች የከተማዋን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ ያላቸው ሚና በየቀኑ እየጎላ መጥቷል።

ኮሚሽኑ እነዚህን አርሶ አደሮች ወደ ባለሃብትነት ለመቀየር የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ከመስጠት ባለፈ፣ ከባንኮች ጋር የብድር ትስስር እንዲፈጥሩ፣ በጋራና በግል እንዲያለሙ ግንዛቤ የመስጠት፣ የሙያ ምክር አገልግሎት መለገስና የፕሮጀክት ማፅደቅ ስራዎችን በቅንጅት እየሰራ ይገኛል።

የአዲስ አበባ ከተማ መስፋፋት በአንድ ወቅት ለአርሶ አደሩ የስጋት ምንጭ የነበረበት ዘመን አክትሞ፣ ዛሬ የዕድልና የብልፅግና በር እየሆነ መጥቷል። የከተማ አስተዳደሩ የጀመረው አርሶ አደርን ከልማቱ ጋር የማስተሳሰር ስራ በትክክለኛ መሬት ላይ ፍሬ እያፈራ መሆኑን እነ አርሶ አደር ለገሰና አርሶ አደር ተስፋዬ ህያው ምስክሮች ናቸው።

ከተማዋ ስትለማ ዙሪያዋን ሳታጠፋ፣ ገበሬውን ሳታፈናቅል በጋራ ማሳደግ እንደምትችል አዲስ አበባ አሁን በተግባር እያሳየች ነው። ይህ ተሞክሮ ተጠናክሮ ከቀጠለ፣ አርሶ አደሮቻችን የከተማዋን የምግብ ፍላጎት ከማሟላት አልፈው የሀገሪቱን የማኑፋክቸሪንግና የኢንቨስትመንት ምሰሶ የመሆን አቅም እንዳላቸው ጥርጥር የለውም። ልማት ማለት ሰውን ያካተተ ለውጥ ነውና፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# መነቀል የጀመረው ማህበራዊ ጠንቅ

- **በበጀት ዓመቱ በባለስልጣኑ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች 28 የምሽት ጭፈራ ቤቶች ታሽገዋል።**
- **ለ2 ሺህ 300 የምሽት ጭፈራ ቤቶች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል።**

**በለይላ መሀመድ**

ወላጅ አባቱ ታምመው ሆስፒታል ገብተው ነበር፡፡ ይህም የተፈጠረው መኖሪያ ቤታቸው ከአንድ ሆቴል ጎን ስለነበር ከሆቴሉ በሚወጣው ከፍተኛ ድምጽ እንደሆነ ይናገራል፤ ወጣት ዳንኤል ሞላ። ወጣቱ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 በተለምዶ 'ላፍቶ በታች' ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ነው፡፡

ቀደም ሲል የንግድ ተቋሙ የሆቴል አገልግሎት ብቻ ይሰጥ የነበረ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ወደ ጭፈራ ቤት በመቀየሩ ለወጣት ዳንኤልና ቤተሰቡ እንዲሁም ለአካባቢው ነዋሪ ከፍተኛ የድምጽ ብክለት ያደርስባቸው እንደነበር ይናገራል፡፡ ከጭፈራ ቤቱ ይወጣ የነበረው ከፍተኛ ጩኸት በተለይም የወላጆቹ መኝታ ቤት ከጭፈራ ቤቱ ጋር በግድግዳ የተያያዘ ስለነበር ሲመሽ ለመተኛት ይቸገሩ እንደነበር ይገልጻል፡፡ ከዚህ ከፍተኛ የድምጽ ብክለት በቂ እንቅልፍ ባለማግኘት ምክንያት ወላጅ አባቱ ለጭንቀት በሽታ ተዳርገው ለህክምና ወደ ሆስፒታል ለመሄድ ተገደው ነበር፡፡

ወጣት ዳንኤልና ሌሎች የቤተሰቡ አባላትም ቢሆኑ በነበረው በከፍተኛ የድምጽ ብክለት ምክንያት በቂ እንቅልፍ መተኛት ባለመቻላቸው ከፍተኛ ድብርት ውስጥ ገብተው እንደነበር ይናገራል። ከንግድ ቤቱ የሚወጣው ድምጽ ህጻናት የተረጋጋ እንቅልፍ እንዳይተኙ ያደርግ ነበር፤ ይባንናሉ፤ ይደነግጣሉ። የአካባቢው ማህበረሰብም የተረጋጋ እንቅልፍ እንዳይተኛ እንቅፋት እንደነበር ወጣቱ አብራርቷል፡፡ ከድምጽ ብክለቱም ባለፈ በመጠጥ ሀይል ተገፋፍተው እርስ በእርስ ስለሚጣሉና ስለሚደባደቡ ድንጋይና ጠርሙስ ወደ ቤታቸውና በራቸው ላይ ይወረወራል፡፡ በስራ ምክንያትም ሆነ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ሳቢያ ወደ ቤት አምሽቶ መግባትም ያስቸግር ነበር፡፡ ግርግሩ ለዘረፋም የተመቻቸ ነበር፡፡ ለዚህ ማህበራዊ ቀውስ መከሰት ምክንያት የሆነው የድምጽ ብክለት ችግር እንዲፈታ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በጋራ በመሆን ቅሬታ ለወረዳውና ለክፍለ ከተማው ማቅረብ በመቻላቸው አሁን ላይ ችግሩ መፈታቱን ይናገራል። ያ የጤናቸው ጠንቅ የነበረው ጭፈራ ቤት በአሁኑ ወቅት የእንግዳ ማረፊያ (ገስት ሀውስ) ሆኗል፡፡

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ነዋሪ የሆኑት አቶ አበበ አድማሱ የመኖሪያ ቤታቸው የተለያዩ የንግድ ተቋማት የሚበዛበት አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የድምጽ ብክለት እንደሚያስቸግራቸው ይገልጻሉ፡፡ ርቀታቸውንና መጠናቸውን ጠብቀው የማይመጡ ድምጾች በመኖሪያ ቤት አካባቢ ላይ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ከባድ እንደሆነ የሚገልጹት አቶ አበበ፣ አእምሯቸው በቂ እረፍት እንዳያገኝ አድርጓቸው እንደነበር ይናገራሉ፡፡ ቤት ውስጥ ተረጋግተው እንዳይቀመጡ እንዲሁም በእንቅልፍ ሰዓት በቂ እንቅልፍ እንዳያገኙ እንቅፋት ሆኖባቸው እንደነበርም ይናገራሉ፡፡

እሳቸውና የአካባቢው ማህበረሰብ በጋራ በመሆን ይረብሻቸው የነበረውን ይህንን የድምጽ ብክለት ለክፍለ ከተማው አካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት እንዲሁም በአካባቢያቸው ማህበረሰብ ለተመረጡ ተወካዮች ቅሬታቸውን በማቅረብ ችግሩ እንዲፈታ አድርገዋል። ጽህፈት ቤቱም የነዋሪውን ቅሬታ ተቀብሎ በሰራው ተከታታይነት ያለው የክትትልና ቁጥጥር ስራ ችግሩ ሙሉ በሙሉ እንደተፈታላቸውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እየኖሩ ስለመሆናቸው ያስረዳሉ። በዚህም ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት የአካባቢ ብክለትና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ቡድን መሪ ፍቃዱ ተሾመ በበኩላቸው፤ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ከድምጽ ብክለት ጋር ተያይዞ በርካታ ቅሬታዎች ማህበረሰቡ ያቀርብ እንደነበር ነው የሚገልጹት፡፡ በየአካባቢው "ሆቴልና ሬስቶራንት" በሚል ስም ይከፈቱ እንጂ አብዛኞቹ የምሽት ክለብ ስራ ስለሚሰሩ ከፍተኛ የድምጽ ብክለት አለ፡፡ ጽህፈት ቤቱ የህብረተሰቡን ቅሬታ ተከትሎ በቀንም ሆነ በምሽት ተከታታይነት ያለው የክትትልና ቁጥጥር ስራ ይሰራል። የድምጽ ብክለት መፍጠራቸው በተረጋገጠባቸው ተቋማት ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ስራን ጨምሮ ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ የገንዘብና ከቦታ እንዲነሱ እንዲሁም የንግድ ፍቃዳቸው እንዲሰረዝ የማድረግ ቅጣት እንዲጣልባቸው በማድረግ እርምጃ ተወስዶባቸዋል። ጽህፈት ቤቱ ወደ እርምጃ ከመግባቱ በፊት ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል። አንዳንድ ተቋማት በተፈጠረላቸው ግንዛቤ መሰረት የሚጠቀሙበትን ጀኔሬተርና ሞንታርቦ ደረጃውን የጠበቀ ሳውድ ፕሩፍ ወይንም ድምጹ ወደ ውጪ ወጥቶ ሰውን በማይረብሽ መልኩ ማድረግ ችለዋል፡፡

በህብረተሰብ ላይ ቅሬታ እየፈጠረ ያለውን ችግር የመለየት ስራ የሚሰራው በሁለት መልኩ ሲሆን አንደኛ በእቅድ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ እና ከማህበረሰብ በሚመጣ ቅሬታ መነሻነት ነው፡፡ እስካሁን በተሰራው የክትትልና ቁጥጥር ስራ በአሁኑ ወቅት ቅሬታው እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ እስከአሁን ድረስ 10 የሚሆኑ ቅሬታዎች ቀርበው ስምንቱ ተፈተዋል፡፡ አብዛኞቹ ችግሩ የተፈታባቸው ተቋማት ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶችና የብሎኬት ማምረቻዎች ናቸው፡፡ ቀሪው ከእምነት ተቋማት ጋር የተያያዘ ከመሆኑ አንጻር ከአዲስ አበባ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን ችግሩን ለመፍታት በሂደት ላይ መሆናቸውንም ነው የሚገልጹት፡፡


በተመሳሳይ በልደታ ክፍለ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ባለሙያ አቶ ተመስገን ወንድማገኝ በክፍለ ከተማው የማህበረሰቡ የቅሬታ ምንጭ የሆነውን የድምጽ ብክለት ችግር ለመፍታት ከድምጽ ጋር ግንኙነት ያላቸው ተቋማት በቀንና በማታ ምን ያህል የድምጽ መጠን (ዴሲ ቢል) መጠቀም እንዳለባቸው ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሰረት የክፍለ ከተማው የአካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት ባለሙያ ማህበረሰቡ ከመረጣቸው ተወካዮች ጋር በጋራ በመሆን ወጥተው ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ በተለያዩ ሚዲያዎች፣ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ ቤት ለቤት በራሪ ወረቀት በመበተንና በማስተማር ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ የድምጽ ብክለት ስታንዳርድ ቤት ለቤት የመለጠፍ ስራም ይሰራል፡፡ ሆቴሎች ድምጽ ወደ ውጭ ወጥቶ ነዋሪን እንዳይረብሽ የሚጠቀሙት ሞንታርቦ ሳውንድ ፕሩፍ እንዲያስገጥሙ ደረጃቸውን የጠበቁ ጀኔሬተሮችን እንዲጠቀሙ በማድረግ የድምጽ ብክለት እንዲቀንስ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ አሁን ላይ የማህበረሰቡ ግንዛቤ እየሰፋ በመምጣቱ ችግሩ የት ሄዶ ሊፈታለት እንደሚችልና ወደ አካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤት እየመጣ ይገኛል። ተቋማትም የድምጽ አጠቃቀማቸውን እያዘመኑና እያሻሻሉ መጥተዋል፡፡ ማህበረሰቡም ከመካከላቸው ይወክሉናል ያሏቸውን ግለሰቦች አምባሳደር በማድረግ ችግሩን በጋራ ለመቀነስ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

## በከተማ ደረጃ የድምጽ ብክለት ችግር ምን ያህል ነው?

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ብክለት ክትትልና ተፅዕኖ ግምገማ ቡድን አስተባባሪ ወይዘሮ ሰናይት ተስፋዬን በከተማ ደረጃ የድምጽ ብክለት ችግር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች እና የመጣውን ለውጥ ለጋዜጣው ዝግጅት ክፍል ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

ቡድን አስተባባሪዋ ገለጻ፤ እንደ ከተማ ማህበረሰቡ በብዛት በቅሬታ ከሚነሱ የብክለት አይነቶች መካከል በስፋት የሚነሳው የድምጽ ብክለት ነው። ይህንን ችግር ለመፍታትም ከክፍለ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤቶች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በየክፍለ ከተማው ከተለያዩ አካባቢዎች የተነሱ የድምጽ ብክለቶች በበጀት ዓመቱ እስካሁን ድረስ ከ200 በላይ ቅሬታዎች ቀርበዋል፡፡ የብክለቱ ምንጭ የሆኑት እንደ ሆቴልና ጭፈራ ቤቶች ያሉ ናቸው፡፡ በተደረገው ጥረትም ቅሬታዎቹን መቀነስ ተችሏል። ይሁን እንጂ የድምጽ ብክለትን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት በባህሪው አስቸጋሪና ፈታኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ከማስጠንቀቂያ ጀምሮ በገንዘብም ይሁን ፍቃዳቸውን እስከመሰረዝ ድረስ ቅጣት የተጣለባቸው ተቋማት ለአንድና ለሁለት ወር ያህል ድምጻቸውን ያጠፉና ወደ ቀደመ ጥፋታቸው ይመለሳሉ፡፡ በተለይም በሆቴል ቤት ስም የሚከፈቱ ጭፈራ ቤቶች ስማቸውንና የመስሪያ ቦታቸውን ቀይረው እንደገና ይጀምራሉ፡፡

አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንም ተግባርና ኃላፊነቱን ከመወጣት አንጻር ተከታታይነት ያለው ስራ በመስራት በተለይም በማህበረሰቡ የሚመጡ ቅሬታዎችን ይፈታል፡፡ በተጨማሪም ባለስልጣኑ በበጀት ዓመቱ በመደበኛ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ይሰራል። በዚህም 28 የምሽት ጭፈራ ቤቶች ታሽገዋል፡፡ በ2 ሺህ 300 የምሽት ጭፈራ ቤቶች ላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የህብረተሰቡን እንግልት ለመቀነስ በሚል ፍቃድ የሚሰጠው በአንላይ ቢሆንም፤ ንግድ ቢሮ ፍቃድ በሚሰጥበት ወቅት ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በቅንጅት መስራት ይኖርበታል፡፡ "አካባቢውና የሚሰጠው አገልግሎት ምን ያህል የተስማማ ነው?" የሚለውን ማወቅ የሚችለው አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በመሆኑ ንግድ ቢሮ ፍቃድ በሚሰጥበት ወቅት ፍቃድ የሚያወጣውን አካል ከባለስልጣኑ ይሁንታን ማግኘቱን ቢያረጋግጥ መልካም እንደሆነ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል፡፡ ከዚህ አንጻር ባለስልጣኑ ከንግድ ቢሮ ጋር ውይይት ማድረጉንም አንስተውልናል፡፡



ፎቶ ከፋይል

በመዲናዋ የድምፅ ብክለት ለመግታት የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ነው

## በአንድ... ከገጽ 5 የዞረ

እንዲሁም አብላጫ ድምፅ ያገኘው አካል መንግሥት መስርቶ ሀገር የሚመራበት ዋነኛ መንገድ ነው። ይህ ሂደትም ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ሰላማዊና ሕጋዊ መስመርን ሲከተል ብቻ ነው፡፡

ሰላማዊ የምርጫ ባህል ሲባል የሕዝብን ውሳኔ የመቀበልና ሕዝብን የማክበር ጉዳይ እንደሆነ ያሬድ (ዶ/ር) ያነሳሉ። በሕዝብ ይሁንታ ላይ የተመሰረተ መንግስትና ሰላማዊ መግባባት የሰፈነባት ሀገር ለመፍጠር ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ የሥልጣን መንበር ላይ ያለው አካል የምርጫው ሂደት ነጻ፣ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የማድረግ ቀዳሚ ኃላፊነት አለበት። የተፎካካሪ ፓርቲዎችም ሀገራችን በብሔር፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ አመለካከት ብዝሃነት ያለባት ሀገር መሆኗን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ወደ ግጭት የሚወስዱ፣ ጥላቻን የሚፈጥሩና የሌላውን ማንነትና ክብር የሚነኩ ድርጊቶችን ከመፈጸም መቆጠብ ይኖርባቸዋል።

ሰላማዊ የምርጫ ባህል ከዴሞክራሲ ባህል ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ የምርጫ ሂደት እንዲኖር በመንግሥት በኩል የሚደረጉ ጥረቶች መልካም መሆናቸውን ያሬድ (ዶ/ር) ያነሳሉ። ይሁንና ዴሞክራሲ የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን በሂደት እየዳበረና እየተረጋገጠ የሚመጣ በመሆኑ፣ የእያንዳንዱ ዜጋ የአስተሳሰብ ድምር ውጤትና የሕዝብ ድጋፍ የሚሻ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የዴሞክራሲ ሥርዓት ስር እንዲሰድ የሁሉም አካላት ትብብር አስፈላጊ መሆኑን የሚገልጹት ምሁሩ፣ ለዚህም በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት የታዩ መልካም ልምዶችን በአብነት ያነሳሉ። በተለይም በመገናኛ ብዙኃን በሚደረጉ ክርክሮች የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለምንም ሥጋት ሐሳባቸውን በነጻነት ሲያቀርቡና የሀሳብ ፍጭት ሲያደርጉ እንዲሁም በከተሞችም በአደባባይ የ“ምረጡኝ” ቅስቀሳ ሲያካሒዱ መታየታቸው፣ መንግሥት ለዴሞክራሲያዊ ግንባታ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡

ሰላማዊና ጤናማ የምርጫ ባህልን ለመገንባት በረጅም ጊዜ ዕቅድ የተለያዩ ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ይጠቁማሉ። በተለይም የዜጎችን ማንነትና ስብዕና በመቅረጽ ረገድ ትልቅ ድርሻ ያላቸው እንደ ቤተሰብ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች እና መገናኛ ብዙኃን ያሉ ተቋማት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል። መንግሥትም እነዚህን ተቋማት በመደገፍና በመምራት፣ ትውልዱ የዴሞክራሲ አስተሳሰብ እንዲላበስ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኢኮኖሚና በተቋማት ግንባታ ላይ መሥራት የዴሞክራሲ ባህልን ለማምጣት እንደሚያግዝ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ያሬድ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

ግሎባል ፒስ ባንክ በተሰኘና በሰላም ግንባታ ዙሪያ በሚሰራ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም የሰላም ግንባታና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር በመሆን እየሰሩ ያሉት የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ምሁሩ አቶ ዳያሞ ዳሌ በበኩላቸው፤ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት ሰላማዊ የምርጫ ባህልን ለመገንባት “የስልጣን ምንጭ ህዝብ ነው” የሚለውን ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን መቀበል፣ ማክበርና ማስረፅ ያስፈልጋል፡፡ ስልጣን መያዝ የሚቻለው በህገ መንግስቱ መሰረት በምርጫና በሰላማዊ መንገድ መሆን አለበት፡፡ ይህንንም ማስረጽና መለማመድ ይገባል፡፡

ከዚህ ባሻገር በእጃችን ላይ ያለውን የምርጫ ዕድል በአግባቡ መጠቀም ይገባል፡፡ ሀገራችን ለመጪው ትውልድ የምትመች፣ ሰላማዊና በኢኮኖሚ የበለጸገች እንድትሆን ከተፈለገ ይህንን በተግባር ማሳየት ይገባል። ተግባራዊ የሚሆንበት አንደኛው መንገድ ደግሞ ምርጫ በመሆኑ፣ በድምፅ መስጫው ዕለት ዜጎች በነቂስ በመውጣት “ሀገሬን ወደፊት ሊያሻግራት የሚችለው መንግሥት ምን ዓይነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ሊኖረው ይገባል?” የሚለውን ጥያቄ በግምት ሳይሆን የፓርቲዎችን ፖሊሲ በአግባቡ በመመርመር ድምፃቸውን መስጠት እንዳለባቸው ያሬድ (ዶ/ር) ያስገነዝባሉ።

7ኛው ጠቅላላ ምርጫ በርካታ ሕዝብ በካርዱ የነገ ሀገሩን ዕድል የሚወስንበት፤ ትርጉሙ ብዙ እንደሆነ የሚያነሱት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ፣ ኢትዮጵያ ከምትገኝበት አካባቢ የተነሳ ከውጭ ሀገሪቱን የማዳከም ፍላጎት ያላቸው ሀገራት አሉ፡፡ ከውስጥም የሚታዩ ችግሮች አሉ። የምርጫ ካርድ ያወጣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ዜጋ በምርጫ ካርዱ ሲወስን ሀገርን ከውስጥና ከውጭ ስጋቶች እየጠበቀ ነው ማለት ነው፡፡ በክፋት በተነሱ ሀይሎች ላይ ድል የመቀዳጀት ጉዳይም ነው፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ ሂደቱን ወደኋላ ከሚመልሱ ማናቸውም ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች በመራቅ መሳተፍ አለበት። ሀገራችን የምትጸናውና ወደፊት የምትራመደው በዴሞክራሲያዊ ሂደት በድምፅ ስንወስን በመሆኑ መብታችን በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል ሲሉ ያሬድ (ዶ/ር) መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

በጥቅሉ 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ መጠናቀቅ ከምንም በላይ የሚጠቅመው ሀገርና ህዝብን በመሆኑ፣ መራጮች በምርጫ ካርድ ህይወታቸውን የሚያሻሽል፤ ህዝብና ሀገርን ወደፊት የሚያሻግር የፖሊሲ አማራጭ አለው ለሚሉት የፖለቲካ ፓርቲ ድምጻቸውን በመስጠት የዜግነት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው እንላለን፡፡

## ተረጂነትን... ከገጽ 6 የዞረ

ግብርና፣ በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ ሥልጠናዎችን እንደየዘርፋቸው የወሰዱ ናቸው፡፡

በመርሐ ግብሩ የአመለካከት፣ የሕይወት ክህሎትና ሙያዊ የሆነ ቴክኒካል ሥልጠናዎች ይሰጧቸዋል፡፡ በባለሙያ የተደገፈ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙም ይደረጋል፡፡ በዋናነትም ትኩረት የሚደረገው በዘላቂነት ኑሯቸውን በሚለውጥ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ነው፡፡

እነዚህ ዜጎች በሚደረግላቸው ድጋፍ ወደ ምርታማነት እንዲሸጋገሩ፣ የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡና አለፍ ሲልም ሌሎችንም እንዲጠቅሙ የማስቻል ሥራ እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች ሦስት ዓመታት በመርሐ ግብሩ ታቅፈው የነበሩና በኮሚቴ በመለየት፣ በሕብረተሰቡ በመተቸት፣ በቅሬታ ኮሚቴ ታይተው የተመረጡ መሆናቸውንም ያነሳሉ፡፡

የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎቹ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ መሆናቸውን ያነሱት አቶ አብርሃም፤ ወደ አምራችነት መሸጋገራቸው የነበረባቸውን ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ጫና በመቅረፍ ለሥራ ያላቸው ፍላጎት እንዲጨምርና ሠርተው እንዲለወጡ ያደርጋቸዋል፡፡ ኢኮኖሚያቸውንም በማሻሻል ራሳቸው ተለውጠው ለሌሎችም የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል ሲሉ የሴፍቲኔትን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያብራራሉ፡፡

እነዚህ የሥራ ዕድል የተመቻቸላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ምርታቸውን ይዘው እንዲወጡ ባዛር ማዘጋጀት፣ ለእነሱም ቅድሚያ መስጠት፣ የተለያዩ ባለሀብቶችን በማነጋገርና ከማይክሮ ፋይናንስ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የማመቻቸት፣ ብድር እንዲወስዱም የማድረግና መሥራት እንዲችሉ ሥልጠና የመስጠት ሥራ እንደሚሠሩም ነው የነገሩን፡፡

በምግብ ዋስትና መርሐ ግብር ታቅፈው ወደ ሥራ የገቡ ዜጎች የወደፊት ሕልማቸውን ለማሳካት በር ከፍቶላቸዋል። ሠርተው እንደሚለወጡም በተግባር አሳይተዋል። ተረጂ ነን ከሚል አስተሳሰብ ወጥተው መሥራት እንደሚችሉና አቅም እንዳላቸው ተረድተውበታል፡፡ ይህ ሲሆን ከራሳቸው አልፈው አገራቸውንም ጭምር የሚጠቅሙ ይሆናሉ ብለዋል አቶ አብርሃም በማጠቃለያቸው፡፡

## በሚሊዮኖች... ከገጽ 10 የዞረ

አዲሱ የፈጠራ ምህዳርም ምስክርነት የሰጠ ነበር። ዴላን ፔጅ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ላይ በመሳተፍ ችግኝ የተከለ ሲሆን፣ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ እድገት ለማየትም በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩቱ ጉብኝት አድርጓል። ይህ መረጃ ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ጥበቃ እስከ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እድገት ድረስ ያላትን እምቅ አቅም በማሳየት፣ የኢትዮጵያን አሁናዊ ገጽታ ለዓለም ያስተዋወቀ አጋጣሚ ሆኗል፡፡

አይሾ ስፒድ የኢትዮጵያን ባህላዊ ልብስ ለብሶና ባህላዊ ምግብ(እንጀራ) እየበላ ያሳየው አዎንታዊ አመለካከት፣ ፍቅርና ደስታ ለኢትዮጵያ ቱሪዝም በገንዘብ የማይተመን ታላቅ ማስታወቂያ ሆኖ አልፏል። የአፍሪካዊው ተጽዕኖ ፈጣሪ ወዲ ማያ እና የቀድሞው የአርሰናል ተጫዋች ባካሪሳኛ ጉብኝትም እንዲሁ። የተለያዩ ዓለም አቀፍ የመዝናኛና የቴክኖሎጂ ሚዲያዎች ሳይቀር ይህንን የኢትዮጵያን ጉብኝት በሰፊው የዘገቡት ሲሆን፣ ይህም የኢትዮጵያን ባህላዊ እሴቶች በቀላሉ በሚሊዮኖች ልብ ውስጥ እንዲሰርጹ በማድረግ ረገድ የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል ሊባል ይችላል፡፡

በተለይ ለአዲስ አበባ ከተማ ይህ ጉብኝት ታላቅ የብራንድ ግንባታ ስራ ነው። የከተማዋ ሰፋፊ የእግር መንገዶች፣ ውብ መናፈሻዎች፣ ደህንነቷና የሌሊት ህይወቷ በሚሊዮኖች ስክሪን ላይ በቀጥታ መታየቱ አዲስ አበባን በአፍሪካ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ብቻ ሳይሆን፣ ለመዝናኛና ለከተማ ቱሪዝም (Urban Tourism) ተመራጭ መሆኗን አስመስክሯል።

ከዚህ በተጨማሪ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን አመለካከት የቀየረ ታላቅ የዲጂታል ዲፕሎማሲ ስራ ነው። የእነዚህ ሰዎች ይዘቶች “Addis Ababa” እና “Ethiopia” የሚሉትን ቃላት በዓለም አቀፍ የዲጂታል ሚዲያ የፍለጋ ድሮች (ሰርች ማድረጊያዎች) ላይ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያደረገ በመሆኑ በተዘዋዋሪ መንገድ የኢትዮጵያን ገጽታ ለዓለም ያስተዋወቀ አጋጣሚ ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ የታዋቂ የይዘት ፈጣሪዎችና የዲጂታል ዜና ዘጋቢ ግለሰቦች ጉብኝት ኢትዮጵያ በዲጂታሉ ዓለም ምን ያህል ትኩረት መሳብ እንደምትችል ያሳየ ትልቅ ማሳያ ነው። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር እይታ (Viral Moment) የፈጠረውን ይህንን አጋጣሚ በቀጣይ ጊዜያት በአዲስ አበባ ብሎም በኢትዮጵያ የቱሪዝም ፍሰት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

በአስር አለቃ አሻግሬ አወቀ ስም የተመዘገበ ነባር ይዞታ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/214/15658/00 የጠፋባቸው መሆኑን በ14/09/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገቡኛል ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ንጉሴ በቀለ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 903 ካርታ ቁጥር 18/19/16997/00 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አለሚቱ ወንድሙ ታችበሌ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060103957 ሴሪ ቁጥር R 0186446 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገቡኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የካርታ ቁጥር የካ2/179940/05 በሴሪ ቁጥር 031752 በውብሸት አበዛ ስም ያለውን ይዞታ አስመልክቶ ይህን ይዞታ በእዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ ይገቡኛል የሚል ተቋምም ሆነ ግለሰብ ወይም ይዞታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው አካል ካለ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ ካርታቸውን እንዲያስረክበን እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ኑርሐሰን ሞሣ ከሊል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር 034966 የሴሪ ቁጥር 025513 የይዞታ ስፋት 94.64 ካ.ሜ የሆነ በስማቸው የተደራጀ ማህደር በማይታወቅ ሁኔታ ከጽ/ቤታችን የጠፋባቸው በመሆኑ ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ማህደር ይገቡኛል የሚል አካል ካለ አስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ማህደር አደራጅተን የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች አብረኸት ረዳ በቀን 5/09/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በራሳቸው ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ለ/ኩ-ራ13/81/5/65264/110/5/00 የሴሪ ቁጥር 1676084 የቤቱ ስፋት በሰነድ 123.1 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገቡኛል አስይገቡኛል የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በልደታ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 4 ቀበሌ 51 በአሁኑ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 207 በልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር (ህብረት ሀይል ነው መረዳጃ ዕድር) በእጃቸው ላይ የሚገኘው የቅድመ ካርታ ኦርጂናል የካርታ ቁጥር ል.8/75/11906/00 የተሰጠበት ቀን 13/10/09 ዓ.ም የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ቅድመ ካርታ ስለጠፋባቸው ይገቡኛል አግኝቼዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በልደታ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎት እና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት እንድታቀርቡ እያሳሰብን በተባለው ጊዜ ውስጥ የማይቀርብ ከሆነ በምትኩ ተለዋጭ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳስባለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የልደታ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የባለይዞታው ስም ቢኒያም ሳሙኤል አለሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 የካርታ ቁጥር ቦሌ12/45/7/6/35-1308/30562/01 ሴሪ ቁጥር 053372 የሆነ ይዞታ በፅህፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ በፅህፈት ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት/ካርታ እንደምንሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ/ ወ/ሮ ወ/ት እነ ጀማነህ አሳመረ ሥማ የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 1 --------ቀበሌ --------- ወይም በቀድሞው ወረዳ ---------- ቀበሌ ------- የቤት ቁጥር ------ የካርታ ቁጥር የካ/207650/10 ሴሪ ቁጥር 0645309 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይገቡኛል የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ውለታ ማሞ ደምሴ በቀን 07/9/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በራሳቸው ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/7/10/4/13/152088/00 የሴሪ ቁጥር 1669077 የቤቱ ስፋት በሰነድ 83.72 ሜ.ካ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ኦርጂናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ምትክ እንዳገኝ ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታውን ወይም ቤቱን በዕዳ ይገቡኛል አስይገቡኛል የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ --- ቀበሌ --- በአዲሱ ወረዳ 09 ቤት ቁጥር --- በካርታ ቁጥር 12/100/4463/00 ለአቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት/እነ አብረኸት ረዳ ተሰጥቷቸው የነበረው ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማናቸውም ምክንያት ይገቡኛል የሚል በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይገቡኛል የሚል ከሌለ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ በሲሳይ አይደኖ አምደግበይ ስም የተመዘገበ ኮንዶሚኒየም ቤት በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 073 የካርታ ቁጥር ኮ/ቀ 03/0021364/00 ሴሪ ቁጥር 1526126 የሆነ ኮንዶሚኒየም ቤት ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን በ20/09/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይገቡኛል ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአራዳ ክ/ከተማ በቀድሞ ወረዳ 2 ቀበሌ 16 በአዲሱ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 016 በወ/ሮ ትዕግስት ሐዋዝ ስም የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር አ/10/07/9453/02 ሴሪ ቁጥር 0662046 ካርታው የተሰጠበት ቀን 0/103/2012 ኦርጂናል ካርታ ከማህደር ክፍል በመጥፋቱ ቀጣይ አገልግሎት ለመስጠት ተቸግረናል፡፡

በመሆኑም አገልግሎቱን ለመስጠት ያመች ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይገቡኛል የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር በአራዳ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲቀርቡ እያሳወቅን ካልቀረቡ ግን አገልግሎቱን የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ በአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**


SIKET BANK
ስኬት አል-ነጃህ
سكيت النجاح
እንኳን ለ1,447ኛው ዒድ አል-አድሃ (አረፋ)
በዓል አደረሳችሁ!
በፍቅር፣ በደስታና በአብሮነት የምታከብሩት
በዓል እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።
ዒድ
ሙባረክ!
8342
www.siketbank.com
info@siketbank.com
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!


ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ.የተ.የግ.ማ
Commercial Nominees Plc
60th
YEARS OF TRUST
60 አመታትን
በታማኝነት
+251111564350
6630
www.commercialnominees.com,
marketing@commercialnominees.com

# በአረንጓዴ ሜዳ ላይ የፈካው ተስፋ

**በሳህሉ ብርሃኑ**





ፎቶ- ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ ተገንብተው ወደ አገልግሎት ከገቡ አዳዲስ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጥቂቶቹ

ምቹ ባልሆኑና ደረጃቸውን ባልጠበቁ ሜዳዎች ስፖርታዊ እንቅስቀሴዎችን ማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ ታሪክ አካል ሆኖ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የቀድሞ ተጫዋቾች የነበሩት እንደ ሳላዲን ሰይድ፣ አዳነ ግርማ፣ ሽመልስ በቀለና ጌታነህ ከበደን መሆንን ህልማቸው ያደረጉ በርካታ አዳጊዎች አቧራ የለበሰ ፊታቸውን እየጠራረጉ ኳስ የሚያንከባልሉባት መዲና ነበረች አዲስ አበባ።

በመዲናዋ ስመጥር የሆኑት እንደ አልማዝዬ ሜዳ፣ መላጣ ሜዳ፣ ብሪሞ እና '15 ሜዳ'ን የመሳሰሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እነዚህ ህልሞች ይጻፉባቸው የነበሩ ገጾች ናቸው። በእርግጥ እነዚህ የስፖርት ስፍራዎች የአዳጊዎቹን ህልም መሬት ለማውረድ ምቹ አልነበሩም፡፡ ለዓመታት አስታዋሽ ስላልነበራቸው አብዛኞቹ ደረጃቸውን ያልጠበቁ፣ የንጽህና ጉድለት ያለባቸው፣ ለአደጋ አጋላጭና አልፎ አልፎም ለአካባቢው ወጣቶች የሱስ ማስተናጋጃ ስፍራ ሆነው አገልግለዋል።

ለማሳያ ያህል በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የሚገኘውና በተለምዶ ጫካ ሜዳ በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ከቀናት በፊት ለአገልግሎት እስከበቃበት እለት ድረስ የብዙ ወጣቶች የህልም ማጨናገፊያ እንጂ የስፖርት ማዘውተሪያ አልነበረም። ከፈራረሰውና ቆሻሻው ከተከመረበት ወንዝ አጠገብ በመገኘቱ ብቻ ሳይሆን፣ አካባቢው የጤና ጠንቅና በምሽት የወንጀለኞች መሸሸጊያ ሆኖ መቆየቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ሜዳው ዛሬ ወደ ዘመናዊ የስፖርት ማዕከልነት ተቀይሮ ሲያየው ደስታውን የገለፀው የሜደው ተጠቃሚ ወጣት ቢኒያም ኃይሉ፣ ያሳለፈውን አስቸገሪ ጊዜ እንዲህ ሲል ያስታውሳል፣ "ይህ ሜዳ ለእኛ ሜዳ ብቻ አልነበረም፤ ማህበራዊ ግንኙነታችንን የምናጠናክርበት መዋያችን ጭምር ነበር። ከወንዙ የሚመጣው መጥፎ ጠረን፣ ጭቃና አቧራ እየማግን ነበር የምንጫወተው።" ይላል፡፡

አያይዞም ከሁሉም በላይ ግን የከፋው ነገር ጀንበር ስትጠልቅ ይህ ቦታ የወንጀለኞች መፈንጫ ይሆናል፤ ሴት እህቶቻችን በዚህ በኩል ለማለፍ ይፈሩ ነበር በማለት ይገልጻል። ትንኮሳውና ስርቆቱ ሜዳውን የፍርሃት ቀጣና አድርጎት ቆይቷል።

ዛሬ ላይ ግን ሁኔታው ሙሉ በሙሉ እየተቀየረ ነው፤ ከጫካ ሜዳ እስከ አልማዝዬ ሜዳ፣ ከሲኤምሲ እስከ ቤቴል ድረስ፣ ከብሪሞ እስከ ባንቢስ ስፖርታዊ ስፍራዎች አስታዋሽ አግኝተዋል። የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ተዘዋውሮ እንደተመለከተው በርካታ መጫወቻ ሜዳዎች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በበጋው ወቅት አቧራማ፣ ክረምት ሲገባ ደግሞ ከመቅፅፈት የሚጨቀዩት ሜዳዎች ዛሬ ላይ መልካቸው ተቀይሮ ዘመናዊ የሜዳ ንጣፍ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ መቀመጫዎችና አጥር ተሰርቶላቸው ለመርገጥ የሚያሳሱ ምቹ የስፖርት ስፍራዎች ሆነዋል፡፡ አብዛኞቹ እንደ አዲስ የተሰሩት ሜዳዎች በምሽት ጨዋታ እንዲደረግ የሚያስችል መብራት ጭምር የተገጠመላቸው ናቸው።

ይህንን የከተማዋን የስፖርት መሰረተ ልማት አብዮት አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አሰግደው ኃይለጊዮርጊስ እንደሚገልፁት ከለውጡ በፊት በከተማዋ የነበሩት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከ400 አይበልጡም ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን በመንግሥት፣ በባለሀብቱና በማህበረሰቡ የተቀናጀ ጥረት ከ2 ሺህ በላይ ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተገንብተው ለአገልግሎት በቅተዋል። ከእነዚህ ማዘውተሪያዎች ውስጥ ከ100 ያላነሱት በኮሪደር ልማት አማካኝነት የተገነቡ ናቸው። ወጣቶች ሁለንተናዊ ስብዕናቸውን እንዲገነቡ የሚያግዙ 114 ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 65ቱ ሙሉ በሙሉ በዘመናዊ መገልገያዎች የተደራጁ ናቸው።

የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የማህበራትና ውድድር ዳይሬክተር አያሌው ታደለ እንደሚገልጹት፣ እነዚህ ስፍራዎች ለከተማዋ ድምቀት ከመሆን ባለፈ የህብረተሰቡን የስፖርት ተጠቃሚነት ያረጋግጣሉ። በተለይ የቅርብ ጊዜዎቹ ግንባታዎች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል እና የስፖርት ዓይነቶች ያካተቱ መሆናቸው ቀደም ሲል ከነበሩት የተለዩ ያደርጋቸዋል። በተለይም የኮሪደር ልማቶች ላይ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተካትተው መሰራታቸው እንደ እግር ኳስና አትሌቲክስ ካሉ ከተለመዱት ውጪ ለሆኑ የስፖርት አይነቶችም ሰፊ ዕድል ፈጥሯል።

የአዲስ አበባ የወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ዋሲሁን እንደሚገልፁት፣ የኮሪደር ልማቱ የቴኳንዶ ስፖርትን ጨምሮ የስኬት ቦርድ ስፖርት ውድድር፣ የቴኳንዶ ፌስቲቫልና ትርዒትን የመሳሰሉ ስፖርታዊ ክንውኖች እንዲለመዱና እንዲስፋፉ ትልቅ አቅም ሆኗል።

ወጣቶችም ይህንን ለውጥ በተግባር እየኖሩት ነው። በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ወጣት ማዕከል ውስጥ በተሰራው ዘመናዊ ሜዳ ላይ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ያገኘነው ወጣት ዮሴፍ አለባቸው ስሜቱን አጋርቶናል። "አሁን ላይ የቅርጫት ኳስና እግር ኳስ የምንጫወተው በምቹ ሜዳዎች ነው። ከዚህ ቀደም ግን በአብዛኛው የምንጫወተው የመኪና መንገድ በመዝጋት በመሆኑ ብዙ ችግሮችን አሳልፈናል፤ ከተሽከርካሪ ጋር እየተጋፋን ራሳችንን ለከፍተኛ አደጋ አጋልጠን ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እናደርግ ነበር። አንዳንድ ጊዜም መጫወቻ ሜዳ ፍለጋ ከአካባቢያችን ርቀን ለመሄድ እንገደድ ነበር።"

ከፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ መገናኛና ቦሌን ይዞ ከተማዋን የሚያካልለው የኮሪደር ልማት ስራ ለስፖርቱ ዘርፍ የሰጠው ትኩረት በስፖርት ወዳዱ ዘንድ ትልቅ ምስጋና አስገኝቶለታል። በገርጂ አካባቢ ነዋሪ የሆነው ወጣት ዋለልኝ ተስፋዬ "ዘወትር እሁድ ስፖርት የመስራት ልምድ አለኝ፤ ከዚህ ቀደም ንጹህና ሰፋፊ አረንጓዴ ስፍራዎችን በመዲናዋ ማግኘት ባለመቻሉ ስፖርት ልንሰራ ወጥተን በሽታ ሸምተን እንመለስ ነበር። ዛሬ ግን ያ ታሪክ ተቀይሯል" ይላል።

ዘመናዊ መብራቶች የተገጠሙላቸው ሜዳዎችና ሰፋፊ የሩጫ መንገዶች መዘጋጀታቸው ስፖርትን የጥቂት ውድድር ወዳዶች ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው ማህበረሰብ የዕለት ተዕለት ባህል እንዲሆን አድርጎታል። ማለዳና ምሽት ላይ ወጣቶችም ሆኑ ነዋሪዎች ንጹህ አየር እየተነፈሱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረጋቸው፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን በመከተል ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ራሳቸውን እንዲጠብቁና በስፖርት ማህበረሰብ እንዲፈጠር እያገዘ ነው።

የመዲናዋ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአብዛኛው መለወጣቸውን የአዲስ ተስፋችን እግር ኳስ ፕሮጀክት መስራችና አሰልጣኝ መሐመድ ናስር ያረጋግጣል። በሲኤምሲ አካባቢ ከ7 እስከ 17 ዓመት ያሉ አዳጊዎችን በፕሮጀክት አቅፎ በማሰልጠን ላይ የሚገኘው አሰልጣኝ መሐመድ፣ የመሰረተ ልማቱ መስፋፋት የስፖርት መነቃቃትን ከመፍጠር ባለፈ ወጣቱ አልባሌ ቦታ እንዳይውል ማድረጉን ያነሳል።

ለውጡ ይዞት የመጣውን ሳይንሳዊ ፋይዳም አሰልጣኙ እንዲህ ሲል ያብራራል አሰልጣኞች ደረጃውን በጠበቀ ስፍራ ማሰልጠን በመጀመራቸው የስፖንሰር ድጋፍና ለስራቸው ተመጣጣኝ ክፍያ ማግኘት መቻላቸውን ይገልጻል። እንደዚሁም ለአዳጊዎች የሚሰጡ ስልጠናዎች ሳይንሳዊና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ የተጫዋቾችን የጉዳት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሶታል።

ደረጃቸውን የጠበቁ ሜዳዎች መሰራታቸው አዳጊዎችን በፕሮጀክት አቅፎ ለሚያሰለጥኑ ባለሙያዎች ሰፊ እድል ፈጥሯል። ታዳጊዎች ከአደጋና ከጉዳት ነጻ በሆነ መልኩ፣ ገና በለጋ እድሜያቸው ሳይንሳዊ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ በማስቻሉ የነገ የሀገር ባለውለታና በአለም አቀፍ መድረክ ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉ ብቁ ተተኪ ስፖርተኞችን ለማፍራት ጠንካራ መሰረት እየጣለ ይገኛል።

እንደ አሰልጣኝ መሐመድ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎቹ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖራቸው በማድረግ ከመንግስት ድጎማ ተላቅቀው ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ መቅደም አለበት። ተቋማቱ በባለሙያ እንዲተዳደሩ፣ ከመጫወቻ ሜዳ ውጪ ያሉ እንደ መጸዳጃ ቤት፣ ፍሳሽ ማስወገጃ እና ልብስ መቀያየሪያዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። ሜዳዎቹን ውሃ የሚያጠጣ፣ እረፍት የሚያገኙበትን ጊዜ የሚቆጣጠርና ጥገና የሚደረግበት የባለሙያ አሰራር ሊዘረጋ ይገባል ባይ ነው።

ይህንን ስጋት ለመቅረፍ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በበኩሉ፣ በከተማዋ የተገነቡ እና እየተገነቡ የሚገኑ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች በህግ እንዲተዳደሩ መመሪያ ማዘጋጀቱን አስታውቋል። በአዲስ መልክ የሚሰሩና ነባር ስፍራዎች ተገቢው ጥበቃ እንዲደረግላቸው ከማዕከል እስከ ወረዳ በቅንጅት መስራት እንዲሁም የሁሉንም ማዘውተሪያዎች መረጃ በአንድ ቋት ማደራጀት የተጠያቂነት ስርዓት ለመዘርጋት ታቅዷል። ይህ አሰራር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎቹን በዘላቂነት ለመጠቀምና እየተነሱ ያሉ የተንከባካቢ እጥረቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመመለስ መፍትሔ እንደሚሆን ይታመናል።


እሁድ ምሽት ከ2፡00 ሰዓት ጀምሮ ይጠብቁን
ሸዊት
ከበደ
ቴዎድሮስ
ተሾመ
ውብ አዲስ
ተስፋዬ
ቢማ
ተስፋዬ
እሸቱ
Addis Media Network
TEDDY STUDIO